# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 104 ታኅሣሥ 14 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# በቀጣይ የበጋ ወራት ሰብል ለመሰብሰብ ምቹ የአየር ሁኔታ እንደሚኖር ኢንስቲትዩቱ ገለጸ

## - እስካሁን 60 ከመቶ ከሚሆነው መሬት ላይ ሰብል ተሰብስቧል

ገመቹ ከድር

አዲስ አበባ ፡- በቀጣይ በጋ ወራት ሰብል ለመሰብሰብ ምቹ አየር ሁኔታ እንደሚኖር የኢትዮጵያ ሜቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ። ግብርና ሚኒስቴር በበኩሉ እስከ አሁን ድረስ በመኸር እርሻ በዘር ከተሸፈነው 13 ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ሄክታር ውስጥ 8 ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር (60 በመቶ ) ሰብል መሰብሰቡን ገልጸዋል ።

በኢትዮጵያ ሜቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሜቲዎሮሎጂ ትንቢያ እና ቅድመ ማስጠንቀቂያ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር አሳምነው ተሾመ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፤ የኢንስቲትዩቱ የትንበያ መረጃዎች በቀጣይ ወራት የሚከሰት የአየር ሁኔታ ሰብል ለመሰብሰብ ምቹ እንደሚሆን አመላክተዋል። ይህ መረጃ እስከ ተጠናከረበት ጊዜ ድረስ ማለትም በጥቅምት እና በኅዳር ወር በአብዛኛው ሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታና ከመደበኛ በታች የዝናብ ስርጭት እንደነበራቸው ገልጸዋል ።

አሁናዊ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ በዓረብ ምድርና በቀይ ባሕር አካባቢ ዝቅተኛ የአየር ግፊት መፈጠርን ምክንያት በማድረግ ወደ ኢትዮጵያ የሚነፍሰው እርጥበት አዘል አየር በተወሰኑ የሀገራችን ክፍሎች የደመና ሽፋን እንዲጨምር አድርጓል። ይህ ክስተት በምሥራቅ አማራ አካባቢ በሁለቱም ሰሜንና ደቡብ ወሎ ዞኖች፣ በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎችና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ደጋማ አካባቢዎች ላይ

በቀጣይ የበጋ ወራት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የሰላም ስምምነቱ ባለሀብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው ለማልማት ያላቸው ፍላጎት እንዲጨምር አድርጓል

## - ኮርፖሬሽኑ ከ11 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ካስመዘገቡ ኩባንያዎች ጋር ውል ተፈራርሟል

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ያለውን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተፈረመው የሰላም ስምምነት የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲያድግና ባለሀብቶችም በኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው ለማልማት ያላቸው ፍላጎት እንዲጨምር ማድረጉን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ። ኮርፖሬሽኑ ከ11 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ካስመዘገቡ ሀገር በቀል ኩባንያዎች ጋር የውል ስምምነት ተፈራርሟል።

የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ በስምምነት ፊርማው ወቅት እንደገለጹት፤ የሰላም ስምምነቱ በኮቪድ 19 እና በጦርነቱ ምክንያት ተቀዛቅዞ የቆየው የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲያድግ አድርጓል። በዚህም የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው ለማልማት ያላቸው ፍላጎት እየጨመረ መጥቷል።

በዚህም ባለፉት ሁለት ወራት በርካታ ባለሀብቶች



ፎቶ - ፀሐይ ንጉሴ

በተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮች ለመሠማራት የሚያስችላቸውን ስምምነት ከኮርፖሬሽኑ ጋር ፈጽመዋል ብለዋል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት ባጋጠሙ ችግሮች አገር በቀል ኩባንያዎችን ማጠናከርና የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንትን ማበረታታት አስፈላጊ መሆኑ ትምህርት የተወሰደበት ነው ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ በቀጣይነትም ሀገር በቀል ኩባንያዎችን ለመደገፍና በስፋት ወደ ኢንቨስትመንት ኢንዲሠማሩ ለማድረግ ይሠራል ብለዋል።

የሰላም ስምምነቱ ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ

ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል::
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia




# የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ስርጭት ከኅዳር ጀምሮ በአማካይ ሰባት በመቶ ደርሷል

## - በቅርቡ የኮቪድ 19 ክትባት በዘመቻ ይሰጣል

ገመቹ ከድር

አዲስ አበባ፡- የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ስርጭት በኅዳርና በታኅሣሥ ወር ሰባት በመቶ መድረሱን ጤና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ ዓለም ከወረርሽኙ ጋር በምትኖርበት በአሁኑ

የኮቪድ-19 ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## የሥነ ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን የሀብት ምዝገባ መረጃን እስካሁን ለሕዝብ ክፍት አላደረገም

- የሕዝብ ዕምባ ጠባቂ ተቋም

## የዕንባ ጠባቂ ትችት አዋጁን ካለመረዳት የመነጨ ነው

- የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

ገጽ 11



አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር
የበረንዳ
ታይልስ
ኤጋ
መደበኛ
ኮልሞ
0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565



## ለሕዳሴው ግድብ

ከ17 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ተሰብስቧል

ገጽ 3

# ማኅበሩ የአዲስ አበባ ወጣቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማጉላት እየሠራ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ወጣቶች ማኅበር በመዲናዋ በሚከናወኑ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የወጣቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማጉላት እየሠራ መሆኑን አስታወቀ።

በትናንትናው ዕለት የማኅበሩ 25ኛ ዓመት ሲከበር የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ወጣት ገዛኸኝ ገብረማሪያም ባደረገው ንግግር፤ ማኅበሩ የተለያዩ ውጣ ውረዶችን በማለፍ የዛሬ የሀገር መሪዎች በኢትዮጵያዊነት ባህል እንዲቀረጹ በማድረግ በርካታ ተግባራትን ማከናወኑን ገልፆ፤ የአዲስ አበባ ወጣቶች በመዲናዋ በሚከናወኑ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ያላቸውን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማጉላት እየሠራ መሆኑን ተናግሯል።

ወጣትነት ለሀገር ግንባታ ዕውቀት የሚቀስምበት እና በፈጠራ አቅም የሚኀለበትበት ዕድሜ መሆኑን በማንሳት፤ ለዚህ ውድ ዕድሜ ዋጋ በመስጠት ጤናማ፣ ብቁና ተወዳዳሪ መሆን ይገባል ሲል አሳስቧል። የተለያዩ ማኅበራዊ ግልጋሎቶችን ለከተማዋ ነዋሪዎች በመስጠት ወጣቶች ሀገር ተረካቢ ብቻ ሳይሆኑ ሀገርን የሚሠሩ ለነገ የታራክ አሻራ የሚጥሉ ዜጎች መሆናቸውን እያስመሰከሩ መሆናቸውን አብራርቷል።

የተሻለ ለውጥ ለማምጣት ወጣቶች መትጋት እንዳለባቸው የጠቆመው ፕሬዚዳንቱ፤ ወጣቶች ለአዳዲስ ሀሳቦች ክፍት የሆነ አዕምሯቸውን በአግባቡ በመጠቀም ከሀገር መሪዎች፣ ከሃይማኖት አባቶች፣ ከተፅዕኖ ፈጣሪዎች እና ከልሂቃን እንዲሁም ከማኅበራዊ ሚዲያ አንቀሳቃሾችና ከሚዲያ አካላት ጋር ለበጎ ሀሳብ መትጋት እንደሚኖርባቸውም አመላክቷል።

በተጨማሪም ወጣቶች በቀና አስተሳሰብ መቅረፅ፣ ለበጎ ፍቃደኝነት ለማገልገል ምቹ ሁኔታዎችን



የአዲስ አበባ ወጣቶች ማኅበር 25ኛ ዓመት በተመለከተ መግለጫ ሲሰጥ

መፍጠር ይገባቸዋል ያለው ፕሬዚዳንቱ፤ ሀሳብ በነፃ የሚገለጥበትን መድረክ በማስፋት ችግሮች በሚፈጠሩበት ጊዜ መፍትሔዎች ላይ አተኩሮ የሚሠሩ መሆን እንዳለባቸው ጠቁሟል።

በተለይ የአዲስ አበባ ወጣቶች የተለያዩ ክበባቶችን አቋቁመው የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን እንዳለባቸው ያብራራው ወጣት ገዛኸኝ፤ የወጣቶች ጊዜ ማሳለፊያ ቦታዎች በማዘመን እና አቻ ለአቻ ውይይቶችን ምህዳር በማስፋት በቴክኖሎጂ የታገዘ ዕውቀት በመስጠት የከተማዋን ብሎም የሀገሪቱን ወጣቶች ተሳታፊና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ሰፋፊ ሥራዎችን ለመሥራት በማኅበሩ በኩል ዝግጅት መደረጉን ተናግሯል።

ማኅበሩ 25ኛ የምሥረታ ዓመት ሲያከብር ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ ከአዲስ አበባ ከተማና ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እና ከሌሎች አጋር አካላት ጋር "የአዲስ አበባ ቀለማት" ፌስቲቫል ለማዘጋጀት ቅድመ ዝግጅቱ መጠናቀቁን እና ፌስቲቫሉ ወጣቶች የፈጠራ ሥራቸውን በተመጣጣኝ ዋጋ ለማኅብረሰቡ በማቅረብ ተጠቃሚ ከማድረጉ ባለፈ የሥራ ዕድልም ይፈጥራል ብሏል።

አዲስ አበባ ቀለማት ፌስቲቫል በማዘጋጀት የአዲስ አበባ ወጣቶች የፈጣራ ሥራቸውን በተመጣጣኝ ዋጋ ለከተማዋ ማኅበረሰብ በማቅረብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረግ ባለፈ በትምህርት፣ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በሥነ ልቦና በማገዝ ጤናማና ንቁ ወጣቶች እንዲፈጠሩ ያደርጋል ሲሉ አብራርተዋል። በዚህም ፌስቲቫል ከሁለት መቶ ሺህ በላይ ወጣቶችን በትምህርትና በሥራ ዕድል ፈጠራ ተጠቃሚ ለማድረግ መታሰቡንም ወጣት ገዛኸኝ አስታውቋል።


አቶ ኢሳያስ ለማ

# ኢትዮጵያ ለምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ስንዴ ለማቅረብ ተዘጋጅታለች

**ሰላማዊት ውቤ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ዘንድሮ በዙሪያዋ ለሚገኙ ኬንያ፤ ደቡብ ሱዳን፤ ጅቡቲን ጨምሮ ለምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት የስንዴ ምርትን መላክ እንደምትጀምር በግብርና ሚኒስቴር የሰብል ልማት ዳይሬክተር አስታወቁ።

አቶ ኢሳያስ ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፤ በአምስት ዓመት ባቀድነው መሠረት በሦስት ዓመት ሀገራዊ ፍላጎቱን እናሳካለን ብለን ግብ በመጣል ተነስተናል። ባለፉት ሦስት ዓመታት የስንዴ ምርት በአርሶ አደሮችና በሰፋፊ እርሻዎች ሲመረት ከነበረበት የመኸር እርሻ በመስኖ ወደ መመረት መሸጋገር ችሏል።

ኢትዮጵያ የስንዴ ምርታማነትን በማሳደግ፤ የምርት ቦታዎችን በማስፋት፤ ሀገራዊ የስንዴ ምርት ፍላጎት ማሳካት ችላለች ያሉት አቶ ኢሳያስ፤ ዘንድሮ ደግሞ የስንዴ ምርትን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ በስፋት እየሠራች ትገኛለች ብለዋል።

እስከ ባለፈው ዓመት ድረስ ኢትዮጵያ የስንዴ ምርትን ከውጪ ስታስገባ ቆይታለች ያሉት አቶ ኢሳያስ፤ ከውጪ የሚገባ የስንዴ ምርትን በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት ከውጭ የሚገባውን ምርት ለማስቀረት ባለፉት ሦስት ዓመታት የስንዴ ምርት ላይ ትኩረት አድርጋ ስትሠራ ቆይታለች ብለዋል።

ኢትዮጵያ የስንዴ ምርትን በየዓመቱ እያሳደገች መምጣቷን በመጠቆምም፤ አምና በልግን ጨምሮ 625 ሺህ ሄክታር ስንዴ መመረቱንና ከዚህ ውስጥ በመስኖ የተመረተው 355 ሺህ ሄክታር መሆኑን ገልፀዋል።

ዘንድሮ ደግሞ አንድ ነጥብ 32 ሚሊዮን ሄክታር በስንዴ ምርት ለመሸፈን እየሠራች መሆኑንም አመልክተው፤ እስከ አሁን ባለው ጊዜም 700 ሺህ ሄክታር መሬት በስንዴ ዘር መሸፈን መቻሉን ተናግረዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ በምርቱ ከሦስት ሚሊዮን በላይ አርሶ አደሮችና ባለሀብቶች ተሳትፈዋል፣ ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ሶማሌና አፋር ክልሎች በምርቱ ላይ የጎላ ተሳትፎ አላቸው። ምርቱ ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን በስፋት ስንዴን ከሚያጠቃው ዋግና ሌሎች ተባዮች መከላከል ላይ በትጋት እየተሠራ ነው።

ምርቱ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራትን በተለይ ጎረቤት አገራትን፤ኬንያ፤ ደቡብ ሱዳንና ጅቡቲን የገበያ መዳረሻነት ታሳቢ ተደርጓል። የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት በሙሉ 100 በመቶ ስንዴ ከውጭ የሚያስገቡ ናቸው። በተለይም ለነዚህ ሀገራት በዋናነት የስንዴ ምርት ያቀርቡ የነበሩት ሩሲያና ዩክሬን ነበሩ።

በፕሪቶሪያ ደቡብ አፍሪካ የተደረገው የሰላም ስምምነት በተለይም በጦርነቱ ምክንያት ከምርት ውጪ የነበሩ 100 የሚጠጉ በየክልሉ ያሉ ወረዳዎች ሙሉ በሙሉ ወደ ምርት ተግባር ፊታቸውን እንዲያዞሩ በማድረግ መልካም አጋጣሚን መፍጠሩን አመልክተዋል።

የአመራሩ ቁርጠኝነት፤ አርሶ አደሩ በስንዴ ራስን የመቻልና በገቢው ፈጥኖ ለመለወጥ ያለው ፍላጎት፤ ይሄንንም ከሉዓላዊነት ጋር ማያያዝና መትጋት እንዲሁም የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ትውልድ የኤክስፖርት የስንዴ ዝርያ በስፋት በኅብረተሰብ ውስጥ መኖሩን ለአብነት አንስተዋል።

# የሕዝቡንና የፖሊስን ትብብር የሚያጠናክር ሀገር አቀፍ ገለልተኛ አማካሪ ቡድን ተመሠረተ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡-የሕዝቡንና የፖሊስን ትብብርና በጋራ መሥራት የሚያጠናክር ሀገር አቀፍ ገለልተኛ አማካሪ ቡድን በይፋ ተመሠረተ።

ሀገር አቀፍ ገለልተኛ አማካሪ ቡድኑ ከመንግሥት አካላትና ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ አካላት ያሉበት ሲሆን የፖሊስ አገልግሎት አሰጣጥን ይበልጥ ለማሳለጥ የሚሠራ መሆኑ ተገልጿል።

የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች እንዲሁም ከሲቪል ማኅበራትና ከሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ አባላትን ያካተተ መሆኑም ታውቋል።

ሀገር አቀፍ ገለልተኛ አማካሪ ቡድኑን የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ጄኔራል በሰብሳቢነት የሚመሩት ሲሆን በፖሊስና ኅብረተሰቡ ዘንድ ትብብርና አብሮነትን ማጠናከር እንዲሁም የፖሊስ አገልግሎት አሰጣጥን ለማሳለጥ ወሳኝ መሆኑ ተመልክቷል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ታገሰ ጫፎ፤ ገለልተኛ አማካሪ ቡድኑ በይፋ መመሥረቱን በትናትናው እለት አብስረዋል። አደረጃጀቱ ወንጀልንና የወንጀል ስጋቶችን በመቀነስ ሂደት የላቀ ጠቀሜታ ይኖረዋል ሲሉም ተናግረዋል።

በተለይ የወንጀል ስጋትን ለመቀነስና ቀድሞ ለመከላከል እንዲሁም በማኅበረሰቡ የአኗኗር ዘይቤ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት



የሚሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

የኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ መሠረተ-ሃሳብ የሆነውን “ፖሊስ የሕዝብ፤ ሕዝብ ደግሞ የፖሊስ” መሆኑን በተግባር የሚያመላክትና የሚያጠናክር አሠራር መፍጠር ያስችላል ተብሏል። በተጨማሪም ሀገር በቀል ማኅበራዊ ሀብቶች፣ እሴቶች እና ባህሎችን ከፖሊሳዊ ሥራ ጋር በማስተሳሰር የኅብረተሰቡን የሕግ ማስከበርና በሰላም የመኖር ዋስትና በመስጠት የጸና የሰላም ባህል ለመገንባትም ጭምር መሆኑ ተመላክቷል።

ፖሊስ ወንጀል ከመፈጸሙ በፊት አስቀድሞ ለመከላከል የሚያስችሉ መረጃዎች፣ አቅጣጫዎችና መፍትሔዎችን በጋራ ማስቀመጥና ሌሎችንም ዓላማ መሠረት ያደረገ ስለመሆኑ ተብራርቷል።

ሀገር አቀፍ ገለልተኛ አማካሪ ቡድኑ ከዚህ ቀደም በክልሎች ደረጃ ተቋቁሞ ውጤት ማስገኘቱ ተገልጿል።

# ለተቀናጀ የኩፍኝ ክትባት ዘመቻ ውጤታማነት ኅብረተሰቡ የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪ ቀረበ

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ለተጀመረው የተቀናጀ የኩፍኝ ክትባት ዘመቻ ውጤታማነት ኅብረተሰቡ የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪ አቀረበ።

የቢሮው ኃላፊ ዶክተር ዮሐንስ ጫላ ዛሬ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንደተናገሩት የዓለምም የኢትዮጵያም ስጋት የሆነው የኩፍኝ በሽታ በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ ክልሎች በወረርሽኝ ደረጃ ተከስቷል። በአዲስ አበባም በተለያዩ ክፍለ ከተሞች በወረርሽኝ መልክ እየተከሰተ ይገኛል። በወቅቱ ክትባት ካልተወሰደ በፍጥነት የሚዛመት በመሆኑ የሚያደርሰው ችግር ከፍተኛ ይሆናል። በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችና የሃይማኖት አባቶች እንዲሁም ሚዲያዎች ለዘመቻው ውጤታማነት የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል።

ክትባቱ ከትናንት ታኅሣሥ 13 እስከ 22 የሚሠጥና ከዘጠኝ ወር እስከ አምስት ዓመት የሆናቸውን ሕጻናት የሚያካትት ሲሆን ከዚህ በፊት ክትባት የወሰዱም ያልወሰዱም የሚከተቡት ይሆናል። እንደ ከተማ ከ520 ሺ. በላይ ለሚሆኑ ሕጻናት ክትባት ለመስጠት ዝግጅት ተጠናቋል። ክትባቱም በከተማዋ ባሉ ሁሉም ጤና ጣቢያዎችና በጊዜያዊነት በተዘጋጁ ተንቀሳቃሽ ማዕከላት የሚሠጥ ሲሆን ከከተማዋ አጎራባች አካባቢዎች የሚመጡትንም የሚያካትት ይሆናል።

በዘመቻው መደበኛ ክትባት ያልጀመሩና ጀምረው ያቋረጡ ልየታ፤ በሕጻናት ላይ የሚታዩ የምግብ እጥረት ልየታና ሪፈራል፤ ለ550 ሺ. ሕጻናት ቫይታሚን ‘ኤ’ እንክብል እደላ እና ለ368 ሺ ሕጻናት የአንጀት ትላትል መድኃኒት እንክብል እደላ እንደሚደረግም ጠቁመዋል።

በተጨማሪ በጨቅላ እድሜ የሚከሰት የእግር መቆልመም የገጠማቸውንና የእናቶችን ከወሊድ ጋር የተያያዘ ፌስቱላ ሪፈራል እንዲሁም የኮቪድ ክትባት ተደራሽ እንደሚደረግ ዶክተር ዮሐንስ ጠቁመዋል። በመሆኑም መላው ኅብረተሰብ ሕጻናትን ከኩፍኝ በሽታ ለመከላከልና አጠቃለይ የማኅበረሰብን ጤና ለመጠበቅ ለሚደረገው ዘመቻ የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል።

# ለሕዳሴው ግድብ ከ17 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ተሰብስቧል

**አማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- የሕዳሴው ግድብ ግንባታ ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን በሀገር ውስጥና በውጪ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሕዝብ ተሳትፎ 17 ቢሊዮን 485 ሚሊዮን 692 ሺ. ብር መሰብሰቡን የዓባይ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት አስታወቀ። ባለፉት አምስት ወራት ከ702 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡም ተጠቁሟል።

የጽሕፈት ቤቱ የሕዝብ ግንኙነትና ሚዲያ ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ኃይሉ አብርሃም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የግድቡ ግንባታ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ በሀገር ውስጥ ቦንድ ሽያጭና ስጦታ ከ15 ቢሊዮን 432 ሚሊዮን 274 ሺ. በላይ ገንዘብ ተሰብስቧል።

በተጨማሪም ከዲያስፖራ ቦንድ ሽያጭ ከ1 ቢሊዮን 394 ሚሊዮን 629 ሺ. ብር በላይ ተሰብስቧል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ዲያስፖራው ለግድቡ የሚያደርገውን ተሳትፎ አሁንም ማጠናከሩን ገልጸዋል።

ከዚህ ባለፈ በ8100 አጭር የጽሑፍ መልዕክት በሦስት ዙሮች በአጠቃላይ ከ658 ሚሊዮን 788 ሺ. 328 ብር በላይ መሰብሰቡን አስታውቀዋል።

ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ በዕቅዱ መሠረት በ2015 በጀት ዓመት ሁለት ቢሊዮን ለመሰብሰብ ውጥን ይዟል። በበጀት ዓመቱ እስከ ኅዳር ወር መጨረሻ ድረስ 702 ሚሊዮን ብር መሰብሰቡን አስረድተዋል።

ከ702 ሚሊዮን ብሩ ውስጥ 576 ሚሊዮን 597 ሺ. 199 ያህሉ ከሀገር ውስጥ ቦንድ ሽያጭ እንዲሁም በስጦታ የተሰበሰበ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከዲያስፖራ ቦንድ ሽያጭና ስጦታ ደግሞ 11 ሚሊዮን 694 ሺ. 857 ብር ፤ በ8100 አጭር የጽሑፍ መልዕክት 51 ሚሊዮን 521 ሺ. 453 ብር በላይ መሰብሰቡን አቶ ኃይሉ ተናግረዋል።

ዲያስፖራው የበለጠ ድጋፍ እንዲያደርግ ጥረት እየተደረገ መሆኑን የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ ከዚህ ቀደም ባንኮች ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ጋር በመሆን ባዘጋጁት የሞባይል መተግበሪያ አማካኝነት ከዲያስፖራው ገንዘብ ገቢ ያደርጉ እንደነበር አስታውሰዋል።

አሁን ላይ ግን በኤምባሲዎችና በቆንስላዎች አማካኝነት እንዲሁም ለዘመድ በመላክ የቦንድና ስጦታ አሰባበሰብ ተግባራት ላይ እየተሳተፈ ነው፤ በመሆኑም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመደገፍ ሀብት በማሰባሰብ ዲያስፖራው ዘንድ ያለውን የተደራሽነት ችግር ለመቅረፍ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል ነው ያሉት።

ለግድቡ ግንባታ ድጋፍ ከ50 ብር ጀምሮ ቦንድ መግዛት ይቻላል ያሉት አቶ ኃይሉ፤ ኅብረተሰቡ ከበፊቱ በበለጠ ለግድቡ ግንባታ የሚያደርገውን ያልተቆጠበ ድጋፍ እንዲያጠናክር ጥሪ አቅርበዋል።

ከግድቡ ግንባታና ድጋፍ ጎን ለጎን የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ ያስፈልጋል ያሉት አቶ ኃይሉ፤ ባለፉት ጊዜያት ደለል ወደ ግድቡ እንዳይገባ የሚያስችሉ ስኬታማ ሥራዎች መከናወናቸው የሚበረታታ መሆኑን ገልጸዋል።

አርሶ አደሩ በበኩሉ በዓባይ ተፋሰስ ላይ እስከ ዛሬ ከ120 ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት የጉልበት፣የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ አከናውኗል ያሉት የጽሕፈት ቤቱ የሕዝብ ግንኙነትና ሚዲያ ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አርሶ አደሩ ይህንን ተግባር አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ብለዋል።

# የሰላም ስምምነቱ ተግባራዊ እንዲሆን ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል

- የትግራይ ምሑራንና ወጣቶች

**ሄርሞን ፍቃዱ**





አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት ተግባራዊ እንዲሆን ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ የትግራይ ምሑራንና ወጣቶች ጠየቁ።

የትግራይ ተወላጅ የሆኑ የመንግሥት አመራሮች፣ ፖለቲከኞች፣ወጣቶች እና ሌሎች ተጋባዥ እንግዶች በተገኙበት የሰላም ስምምነቱ አተገባበር ዙሪያ ለሦስት ተከታታይ ቀናት በአዲስ አበባ የምክክር መድረክ ተካሂዷል።

በውይይት መድረኩ “ያልተሄደበት መንገድ” በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረቡት አቶ ዛዲግ አብርሃ እንደገለጹት፣እያንዳንዱ ዜጋ ለተጀመረው ሁለንተናዊ የለውጥ ሂደት መዘጋጀትና ለተግባራዊነቱ መረባረብ ያስፈልጋል። በተለይም ትግራዋይ ለዘላቂ ሰላም ብሎም የተፈጠረውን ምቹ የፖለቲካ ምህዳር ለማስፋት ሁሉም ድርሻውን በተገቢው መንገድ መወጣት አለበት።

የሰላም ስምምነቱ ዘለቄታዊ አተገባበርን በሚመለከት ሰፊ ውይይት የተካሄደ ሲሆን በተለይም ከክልሉ ውጪ የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች ለውጡን በመደገፍ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን፤የተረጋጋ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች በትግራይ ክልል እንዲኖሩ ሁሉም ወደ ሥራ በመግባት ኃላፊነቱን እንዲወጣ ስምምነት ላይ ደርሰዋል።

ተሳታፊዎቹ፣በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ በጥልቀት ከተወያዩ በኋላ በፕሪቶሪያ የተደረገው የሰላም ስምምነት በመደገፍ ለቀጣይ ድርሻቸውን የሚወጡ መሆናቸውን ገልጸው፤ ቀደም ሲልም የተለያዩ ሀገራዊ ሥራዎች ለምሳሌ የ”#NO MORE” እንቅስቃሴ እና በሚዲያዎች በመሳተፍ እንዲሁም ከመከላከያ ሠራዊት ጎን በመቆም ሀገራዊ ግዴታቸው ሲወጡ መቆየታቸው አስታውሰዋል።

በክልሉ የወደሙ መሠረተ ልማቶች እና ማኅበራዊ አገልግሎቶች መልሶ ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ግንባር ቀደም ሚና ለመጫወት ዝግጁ መሆናቸውን የገለጹት ተሰብሳቢዎቹ፤ የሚደረገው እንቅስቃሴ ስኬታማ እንዲሆን ብሎም የክልሉ ሰላምና ፀጥታ አስተማማኝ እንዲሆንና ሕዝቡ ወደ ቀድሞ ሕይወቱ እንዲመለስ የሰላም ስምምነቱ ተግባራዊ ማድረግ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ጠይቀዋል።

የመከላከያ ሚኒስትሩ ዶክተር አብርሃም በላይ የትግራይ የለውጥ ኃይሉ ሕዝቡን ከመከራ ለመታደግ የከፈለው መስዋዕትነት እጅግ የሚደነቅ መሆኑን ተናግረው፤ አሁንም ቢሆን የትግራይ ሕዝብ ሰላሙ ተረጋግጦ የተሻለ ኑሮ እንዲኖር የጋራ ጥረት እንደሚያስፈልግ መክረዋል።

የቀድሞ የመቀሌ ከተማ ከንቲባ አቶ አታኽልቲ ኃይለሥላሴ በበኩላቸው፣ ቀደም ሲል ከተፈጠሩ አስተዳደራዊ ችግሮች ትምህርት በመውሰድ ለቀጣይ ከመንግሥት ጋር በመሆን ሕዝቡን የለውጡ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚጠበቅባቸውን ድርሻ እንደሚወጣ አስገንዝበዋል።

በተለያየ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኙ የትግራይ ተወላጆች እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ በነፃነት ከሌላው ወንድም ሕዝብ ጋር በወንድማማችነትና በእኩልነት እንዲኖሩ ትግራዋይ የለውጥ ኃይሎች ኃላፊነታቸውን በተገቢው ለመወጣት ዝግጁ መሆናቸውን ተስማምተዋል።

በመጨረሻም የመድረኩ ተሳታፊዎቹ ባለ ስምንት ነጥብ የአቋም መግለጫ በማውጣት የቀጣይ አቅጣጫ በማስቀመጥ መድረኩን አጠናቅቀዋል።

ዜና

# በቀጣይ የበጋ ወራት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የደመና ሽፋን መጨመሩን የትንበያ መረጃዎች አመላክተዋል ።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገራችን ክፍሎች ሌሊትና ማለዳ ቅዝቃዜ ከመጨመሩ ጋር ተያይዞ የቀን ሙቀት መጠን በምሥራቅ አማራ በደብረ ብርሃን፣ ወገል ጤና ፣አምባ ማሪያምና በደባርቅ ከአምስት ዲግሪ ሴልሽስ በታች ተመዝግቧል ። በመካከለኛው ሀገሪቱ ክፍሎች በተለይ በአዲስ አበባ ስድስት ዲግሪ ሴልሽስ፣ በቡኢ አራት ነጥብ አምስት ዲግሪ ሴልሽስ፣ በሐረር ሁለት ነጥብ ሁለት ሴልሽስ ፣ በባሌ ሮቤ አራት ዲግሪ ሴልሽስ የሙቀት መጠን እንደነበራቸው ገልጸዋል ።

በአጠቃላይ ባለፈው በጋ ሁለት ወራት አብዛኛው የሀገራችን አካባቢዎች ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታና አመዘኖባቸው ተስተውሏል ያሉት ዶክተር አሳምነው በቀጣይ ቀናት በተመሳሳይ ሁኔታ ይቀጥላል ብለዋል።

በምሥራቅ አማራ ፣መካከለኛው ሀገራችን አካባቢዎች ፣ሐረርና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ደጋማ አካባቢዎች የሌሊትና ማለዳው ቅዝቃዜ በአንጻራዊ መልኩ ቀጣይነት ይኖረዋል ሲሉም ጠቁመዋል ።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በመጪዎች ሦስትና አራት ቀናት ሰብል ለመሰብሰብ አሉታዊ ተፅዕኖ የማያሳድር እጅግ በጣም አነስተኛ የሆነ የዝናብ መጠን በምሥራቅ አማራ፣ በመካከለኛውና በደቡብ ደጋማ አካባቢዎች ዝናብ እንደሚጠበቅ ገልጸዋል። በጥር ወር ተመሳሳይ የአየር ሁኔታ ስለሚጠበቅ የመኸር ሰብል ለመሰብሰብ ሰፊ ምቹ የአየር ሁኔታዎች እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች አመላክተዋል ።

ኅብረተሰቡ የደረሱ ሰብሎችን በመሰብሰብ ፣ የተሰበሰበውን ሰብል ቶሎ በመውቃት ወደ ጎተራ የሚወስዱበት ሁኔታዎች እንዲያመቻቹ የጠቆሙት ኃላፊው፤ ተለዋጭ አየር ሁኔታዎች ካሉ የኢትዮጵያ ሜቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ስለሚገልጽ ኅብረተሰቡ መረጃውን በመከታተል አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል ።

በግብርና ሚኒስቴር ሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ አበራ ለማ በበኩላቸው እስከ አሁን በተደረገው ሰብል አሰባሰብ ሂደት አልፎ አልፎ የደመና ክምችት ቢኖርም የሰብል አሰባሰቡ ሂደት በተቀመጠለት ሁኔታ ተግባራዊ እየተደረገ ነው ብለዋል።

በመኸር እርሻው በዘር ከተሸፈነው 13 ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥም እስካሁን ድረስ 8 ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር (60 በመቶ) ሰብል መሰብሰቡን አያይዘው ገልጸዋል ።

# የኮቪድ-19 ወረርሽኝ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ወቅት ኅብረተሰቡ ጥንቃቄዎችን ማድረግ እንደሚገባውም ገልጸዋል።

በጤና ሚኒስቴር የኮቪድ-19 ግብረ ኃይል አስተባባሪ ዶክተር መብራቱ መሴቦ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፤ የኮቪድ -19 ወረርሽኝ ስርጭት ከኅዳር እስከ ታኅሣሥ ወር ድረስ ሰባት በመቶ ጭማሪ አሳይቷል ። ስርጭቱ ላለፉት ሰባት ወራት ከአንድ በመቶ እንዳልበለጠም ገልጸዋል።

የዛሬ ሦስት ዓመት ገደማ በቻይና ዩዋን ግዛት ከተከሰተ በኋላ የወረርሽኙን መስፋፋት ተከትሎ ዓለም ከወረርሽኙ ጋር እየኖረች በመሆኑ ኅብረተሰቡ ከወረርሽኙ ጋር በመኖር የሚደረጉ ጥንቃቄዎች ሳይዘናጋ የራሱን ጤና መጠበቅ አለበት ብለዋል ።

እንደ ዶክተር መብራቱ መሴቦ ገለጻ ፤ የኮቪድ-19 ስርጭት መጠን በአሁኑ ሰዓት እንደመጀመሪያው ጊዜ ባይሆንም ንግድ ሥራ ፣ አየር በረራዎች ክፍት ተደርጎ ኅብረተሰቡ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ከወረርሽኙ ጋር ለመኖር ጥረት እያደረገ ነው። ክትባት መስጠት ከተጀመረበት ጊዜ ወዲህ የስርጭት መጠኑ ቢቀንስም ሙሉ በሙሉ አለመጥፋቱን ኅብረተሰቡ ሊገነዘብ ይገባል ብለዋል።

በአሁኑ ወቅትም የአየር ሁኔታውን መቀየር ተከትሎ ማታ ከፍተኛ ቅዝቃዜና ቀን ከፍተኛ ሙቀት በመሆኑ ለኮቪድ-19 ወረርሽኝ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ጉንፋንና መሰል በሽታዎችን መከሰት ምቹ ሁኔታዎች ፈጥሯል። ከዚህም የተነሳ በተወሰነ ደረጃ የስርጭት መጠኑ እየጨመረ ነው ሲሉም መንስኤውን ተናግረዋል ።

ከክረምት ወደ በጋ ሽግግር በሚደረግበት ወቅት ሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ ከፍተኛ ቅዝቃዜ የሚፈጠርበት ወቅት በመሆኑ ወደ ሀገራችን ተሻግሮ በመምጣት በተለምዶ በኅዳርና በታኅሣሥ የሚከሰት ሁኔታ ነዉ። ይህንን መሠረት በማድረግ ኮቪድ-19 ወረርሽኝ ብቻ ሳይሆን ኢንፍሉዌንዛና የተወሰኑ ሌሎችም ተጨማሪ ቫይረሶች በመኖራቸው ሰሞኑን የኢንፌክሽን መጠን እየጨመረ ነው ብለዋል ።

ላለፉት ሰባት ወራት በኮቪድ-19 የተያዙ የሰዎች ቁጥር ከአንድ ፐርሰንት በላይ አይሆንም ያሉት ዶክተር መብራቱ ከኅዳር ወር እስከ ታኅሣሥ በሰባት በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። ኮቪድ-19 ወረርሽኝ እንደ ቲቢና ሌሎች በሽታዎች ከኅብረተሰቡ ጋር አብሮ በመኖር ላይ ስለሚገኝ ኅብረተሰቡ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ አስፈላጊውን ግንዛቤ በመፍጠር ክትባት ማጠናከር ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራበት ነው ሲሉም ጠቁመዋል።

እንደ ሀገር እስከ አሁን ድረስ በተሰጠው ክትባት ለ43 ሚሊዮን ዜጎች ክትባት ተሰጥቷል፤ ከነዚህም ውስጥ 35 ሚሊዮኑ መውሰድ የሚገባቸውን የኮቪድ ክትባት ማጠናቀቃቸውን ገልጸዋል። ክትባቱ የሚሞቱና ሆስፒታል ገብተው የሚታከሙ ሰዎች ቁጥር እንዲቀንስ ማድረጉን ጠቅሰው ያልተከተቡ ሰዎች ለከፋ ሕመም እና ሞት እየዳረጉ እንደሆነም ተናግረዋል።

በሽታ የመከላከል አቅማቸው አነስተኛ የሆኑና ዕድሜያቸው ከ60 በላይ የሆኑ ሰዎች ክትባት መውሰድ ይገባቸዋል ያሉት ዶክተር መብራቱ ሁሉም ሰው ራሱን ለመከላከል ሰዎች ከሚበዙባቸው ቦታዎች መቆጠብ፣ አፍ መሸፈኛ መጠቀም ፣ ምርመራ ማድረግ እና ክትባት እንዲወስዱ መክረዋል። በቅርቡ የክትባት ዘመቻ እንደሚደረግም አያይዘው ገልጸዋል ።




# ርዕሰ አንቀፅ

## የትግራይ ሕዝብ ካለበት ችግር ፈጥኖ ለመውጣት የሚያስችለውን የሰላም መንገድ አጥብቆ ይፈልጋል!

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ላለፉት ሁለት ዓመታት በተካሄደው ጦርነት ዋነኛ ተጎጂ ከሆኑት ውስጥ አንዱ የትግራይ ሕዝብ ነው። ሕዝቡ በጦርነቱ በብዙ ተስፋ እና ዋጋ ያሳደጋቸውን ልጆቹን አጥቷል፤ ከፍ ላለ የንብረት ውድመት ተዳርጓል። የደረሰበትም የስነ ልቦና ጫና ከፍ ያለ ነው።

በእነዚህ ሁለት ዓመታት የጥይት ድምጽ በሚፈጥረው ሰቀቀን ውስጥ ለማለፍ ተገድዷል ፤ በዚህም ሰላምና መረጋጋት አጥቷል ፤ ስለነገዎቹ በርግጠኝነት ማሰብ የሚያስችለውን አቅሙን ተነጥቋል፤ ሰርቶ መብላት፤ የሰላምና እፎይታ ሕይወት ናፍቆታል።

ሕዝቡ ከአንድ ጦርነት እና ጦርነቱ ከፈጠረው ጠባሳ ሳያገግም ወደ ሌላ ጦርነት እየገባ ያለበት እውነታ ፣ እንደ ሕዝብ እያስከፈለው ያለው ዋጋ የከፋ ፣ ስለ ነገዎቹ ሊኖረው የሚችለውን ተስፋ ያጨለመ ፤ስለ ሰላም አብዝቶ እንዲጮህ ያስገደደው ነው።

ከትናንት ሆነ ከዛሬ የህይወት ተሞክሮው የትግራይ ሕዝብ ከሰላም የገዘፈ ወቅታዊ ጥያቄ የለውም። ሊኖር ይችላል ብሎ ማሰብም፤ ሕዝቡ ትርጉም ለሌላቸው ጦርነቶች የከፈለውን ዋጋ አሳንሶ ከማየት የሚመነጭ ህሳቤ ነው።

ይህ ህሳቤ የትግራይ ሕዝብ እንደ ሕዝብ በእጁ ያሉ /በትውልዶች መካከል የተገነቡ መንፈሳዊ ፣ ባህላዊና ማህበራዊ የሰላም እሴቶችን ከልቡ በማውጣት ፤ የጥፋት አጀንዳዎች ማስፈጸሚያ አድርጎ የመጠቀም መሻት አካል ነው።

ከዚህ በላይ የክልሉ ሕዝብ እንደ ሕዝብ ከሰላምና ከሰላም የሚገኙ ትሩፋቶች ተጠቃሚ በመሆን ስለነገዎቹ የተሻለ ተስፋ ባለቤት እንዳይሆን፤ ተስፋ ቢስ ሆኖ ዘመናትን በተሰበረ ልብ በቁዘማ እንዲኳዝ የመፈለግ የክፉዎች ልብ ሴራ ነው።

ይህ ከትግራይ ሕዝብም ባለፈ እንደ ሀገር ሃገርን ሰላም የማሳጣትና የማፍረስ የታሪካዊ ጠላቶቻችን ዘመናት ያስቆጠረ እኩይ ዓላማ አካል የሆነው የእብደት አሳቤ ፤ላለፉት ሁለት ዓመታት ሃገር እና ሕዝብን ጭምር ያስከፈለው ዋጋ ከፍ ያለ ነው።

የትግራይ ሕዝብ ትናንት ሆነ ዛሬ፤ ነገም ቢሆን ከተገነባበት መንፈሳዊ ፣ ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶች አንጻር ስለ ሰላም የነበረው፣ ያለውና የሚኖረው አስተሳሰብ የጸና ነው። የሚፈልገውም ይህን የጸና አስተሳሰቡን የሚያበለጽግለት፤ በተሻለ አቅም ወደቀጣይ ትውልዶች የሚያሻግርለት ነው።

ሕዝቡ መጪዎቹ ትውልዶች ትርጉም አልባ ለሆኑ ጦርነቶች ሕይወታቸውን ፣ ዘመናቸውን እና ተስፋቸውን እንዲገብሩ አይፈልግም። ይህ ዓይነቱ ርግማን ዛሬ ላይ አብቅቶ ፤ መጪዎቹ ትውልዶች ከጦርነት ስጋትና ጦርነት ከሚያስከፍለው ዋጋ ነጻ ሆነው በሰላም የተሻለ ሕይወት እንዲመሩ ምኞቱ ነው።

ከጦርነትና ከጦርነት ወሬ ፤ ከጦርነትና ከጦርነት ጉሰማ ፤ከጦርነትና ከጥይት ድምጽ ነፃ የሆነች ትግራይን ብቻ ሳይሆን ፤ከጦርነት ፉከራና እና ቀረርቶ ልቦና አእምሮው ያልተያዘ ፤ የሰላምና የፍቅር ዜማ የሚያዜም ፤ይህም መለያው የሆነ ትውልድ ለማየት ተስፋው ትልቅ ነው።

በታሪክ እና በመልክዓ-ምድር ፤ በባህል እና በሃይማኖት ከሚመሳሰላቸው፤ ዘመናትን በክፉም በደጉም አብሮ ከኖራቸው ሌሎች ሕዝቦች ጋር መጪዎቹ ትውልዶች በፍቅርና ከዚህ በሚመነጭ መከባበርና መቻቻል አብሮ መኖር የሚችልበትን የአስተሳሰብ መሰረት ማጠንከር ይፈልጋል።

ከዚህ ተጨባጭ እውነታ አንጻር ስለ ትግራይ ሕዝብም ሆነ ስለ ቀጣይ ትውልድ ያሳስበኛል የሚል ቡድንም ሆነ ግለሰብ የሕዝቡን የሰላም መሻት ታሳቢ ባደረገ መንገድ ሊንቀሳቀስ፤ እንደቀደሙት ዘመናት መጪው ትውልድ የጦርነት ገፈት ቀማሽ ሳይሆኑ ከሰላም የሚገኝ ልማት ትሩፋት ተካፋይ መሆን የሚችሉበትን የአስተሳሰብ መሰረት ሊኖረው ይገባል።

ትናንትም ሆነ ከትናንት ወዲያ ሕዝቡን እንደ ሕዝብ ከፍ ያለ ዋጋ ካስከፈሉ የማይጠቅሙ እሳቤዎች በመውጣት፤ እሳቤዎች የፈጠሩትን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ፈጥኖ ማከም ወደሚያስችል የፈውስ መንገድ መጓዝ ፤ለዚህ የሚሆን ቁርጠኝነት መፍጠር ይጠይቃል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## መገናኛ ብዙኃን ለአገር ሰላም

ክብረ ነገስት

በ2012 ዓ.ም ነሐሴ ወር ላይ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን አሰራርና ያሉበትን ሁኔታ ተመልክቶ የዘርፉን ፖሊሲ አሻሽሎ አጽድቋል። ፖሊሲው በዋናነት መሰረት ያደረገውም ከህትመትና ከብሮድካስት ሚዲያው በሻገር ከዚህ ቀደም በመገናኛ ብዙኃን ሕጎች ላይ ያልነበሩትን በበይነ መረብ አማካኝነት የሚሰራጨውን የኦንላይን ሚዲያንና እና የማህበራዊ ሚዲያን እንደ መገናኛ ብዙኃን ዘርፍ በማካተት ተጠያቂነት እንዲኖራቸው በማድረግ ነው::

ይል መልካም ነገር ነው:: ምክንያቱም ዛሬ ላይ እንደ አገር ስናየው ከመደበኛዎቹ መገናኛ ብዚኃን በላይ ማህበራዊ ሚዲያው የህብረተሰቡን ቀልብ በመሳቡ በሚያሰራጨው መረጃም ነገሮችን ከቁጥጥር ውጪ ሲያደርጋቸው ይታያል:: በተለይም ግጭቶችን ከማፋፋም አኳያ ጉልህ ሚና ነበረው:: እናም ይህንን እልባት ለመስጠት በፖሊሲው ላይ የኢትዮጵያ ሚዲያ ምን ዓይነት መልክ ሊኖረው ይገባል፤ አቅጣጫው ወዴት መሄድ አለበት፣ የመንግሥት ድጋፍ ምን ድረስ ሊሆን ይገባል፤ እና መሰል ነገሮችን አካትቶ በአዋጅ መልክ እንዲወጣ ሆኗል:: ይህ ደግሞ በርካታ ችግሮችን የፈታና መፍትሄ የቸረ እንደነበር በጥቂቱም ቢሆን ታይቷል:: እስከመጨረሻው ዘልቋል ወይ ከተባለ ግን ጥያቄ አለበት:: ምክንያቱም ዛሬም ላይ ብዙ ሚዲያዎች ይህንን አጸያፊ ተግባራቸውን ሲከውኑ ይስተዋላልና::

በአዲሱ አዋጅ ብሮድካስት ሚዲያዎች በይዘታቸው እስከ 80 ከመቶ የሚሆነው አገራዊ ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩር ያስገድዳል:: ይሁን እንጂ የሰሞንኛ ወሬያችንን ብቻ ስናነሳ የውጪው የእግር ኳስ ጉዳይ በስፋት ይዞታል:: መዝናናትና መልካም ነገሮችን በሕዝብ ልቦና ላይ መፍጠር መልካም ቢሆንም ጉዳያችን እርሱ ብቻ ነው ወይ? ሲባል ግን መልሱ አይደለም ነው:: ከዚያ የሚቀድሙ ብዙ ልናሳያቸው የሚገቡን ነገሮች አሉ:: ለምሳሌ፣ በሰሜን ኢትዮጵያ የነበረውን ግጭት ለማስቆም የተደረሰው ስምምነት ጋር ተያይዞ ምን ምን አይነት ለውጦች እየመጡ ነው፤ ምንስ ይቀራል፤ ማን ምን ማድረግ አለበት የሚለው ጉዳይ በስፋት ልንዘግበው የሚገባ ነበር:: ሆኖም በዚህ ዙሪያ በጣም ጥቂት ሥራዎች ብቻ ይስተዋላሉ::

የውጪ ሚዲያዎችም ቢሆኑ ይህንን የሰላም ሂደት ችላ ብለውታል:: ምክንያቱም ይህ ለእነርሱ ጉዳያቸው አይደለም:: ለእነርሱ ዘገባና የገቢ ምንጭ የሚሆነው ግጭት ብቻ ነው:: በዚህ ዘገባቸው ደግሞ ከዚህ በፊት የነበሩትን ብቻ ማንሳት ይቻላል:: የየቀኑ ዜና መክፈቻቸው ኢትዮጵያ ነበረች:: ለብዙዎች የመሰብሰቢያ አጀንዳ እስከመሆንም ደርሳለች:: ዛሬስ ከተባለ ጸጥ ረጭ ብሏል:: ምክንያቱም ኢትዮጵያ አሸንፋለች፤ የፈረሰውን እየገነባች ወደፊት እየተራመደች ነው:: በስንዴውም በግዙፎቹ ፕሮጀክቶቿም እየላቀች ነው:: ታዲያ ይህ ለእነርሱ ምን ገቢ ያመጣል፤ እንዴትስ ጉዳያቸው ይሆናል?

አሁን ጉዳዩ መሆን ያለበት የአገር ውስጥ ሚዲያው ነው:: ምክንያቱም ትርፉ የአገር ጉዳይ እንጂ ሌላ አይደለም:: ውጪው ጭምር እንዲደነቅና ዝም እንዳይል ማድረግ ያለበት እርሱ ብቻ ነው:: አሁን አገሪቱ ካለችበት ችግር የሚያላቅቀውን ድጋፍ ማስገኘት የሚችለው መሬት ላይ ያለውን እውነታ ሲያስረዳ ብቻ ነው:: ስምምነቱ ያመጣውን ለውጥና ወደፊት ለመሄድ ምን እንደሚያስፈልግ ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ ማሳየት አለበት:: የኢትዮጵያን የለውጥ ምዕራፍ ዘግቦ ይህቺ ናት ኢትዮጵያ ሊል ይገባል:: የዚያን ጊዜ ውጪ ላይ ያለው ማህበረሰብ ሚዲያውን መከተል ይጀምራል:: ይሄኔ የውጪው ሚዲያም ቢሆን ምርጫ ስለማይኖረው ስለ ኢትዮጵያ መልካም ነገሮችን መዘገቡ ይጀምራል::

ለዚህ ደግሞ እንደአገር ጥሩ ነገሮች ተፈጥረዋል:: አንደኛው ለአገር እድገትና ግንባታ የሚጫወተውን ሚና ከፍ ለማድረግ የሙያውን ነጻነት መጠበቅና በመርህ መመራት እንዲችል መንገዶች ተከፍተውለታል:: ይሁንና አሁንም ከህዝብ ይልቅ ቡድኖችን ማዕከል ማድረጋቸው ለሙያው ዕድገት መቀጨጭ አይነተኛ ሚና እየተጫወተ ነው:: እና ምን ይሁን ከተባለ ሰሞኑን የተሰማው ዜና አስደሳች ነገርን ይዞ ብቅ ያለ ይመስላል:: ይህም መገናኛ ብዙኃን ከሰላም ስምምነቱ ጋር የተያያዙ ዘገባዎችን በምን መልኩ መሥራት እንዳለባቸው የሚጠቁም መመሪያ እየተዘጋጀ መሆኑ ተሰምቷል::

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን እንዳስታወቀው በሰላም ስምምነቱ ከተጠቀሱ ጉዳዮች አንዱ ስምምነቱን ከሚረብሹ ዘገባዎች መታቀብ የሚለው ይገኝበታል። እንዲሁም የሰላም ስምምነቱን ተከትለው የሚወጡ ዘገባዎችም በመልካም እይታና በሚገባቸው ልክ መዘገብ አለባቸው ይላል:: የሰላም ሀሳቦች በምን መልኩ መሰራት እንዳለባቸው የሚጠቁም፣ ለተቋማቱ አቅም የሚፈጥርና እንደ ማጣቀሻ ሊጠቀሙበት የሚችል መመሪያም ተዘጋጅቷልና ከዚህ በኋላ ሁሉም መገናኛ ብዙኃን ከሰላም ስምምነቱ ጋር የተያያዙ ዘገባዎችን ሲሰሩ ሀሰተኛና የጥላቻ ንግግሮችን የያዘ አይሆንም:: ምክንያቱም መመሪያው በሰላም ስምምነቱ የተቀመጠውን ግዴታ መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው።

መመሪያውን መነሻ በማድረግም ባለስልጣኑ ሁሉም መገናኛ ብዙኃን የሚኖራቸውን የሞራል፣ የሙያና ሕጋዊ ግዴታዎችን አክበረው እንዲሠሩ በየጊዜው ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል:: የማስተካከልና ወደ ትክክለኛው መስመር እንዲመጡም ያስችላል:: ከምንም በላይ ሁሉም መገናኛ ብዙኃን የሰላም ግንባታ ላይ የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲወጡ ያግዛል:: ምክንያቱም የሰላም ጉዳይ የሕዘብ ጉዳይ ነው:: መገናኛ ብዙኃን ደግሞ ሁሉ ነገራቸው ሕዝባዊ ነው::

እናም በሰላም መረጋገጥ ላይ መገናኛ ብዙኃን የሚኖራቸው ሚና የማይተካ ሊሆን ይገባል:: ለዚህ ደግሞ ከሙያዊ ሥነምግባርና ከሞራልም ጭምር የሚመነጭ ሥራም ሊሰሩ ይገባል:: የመገናኛ ብዙኃን ሚና የሰላም ስምምነቱ ተሳክቶ ወደ ልማት ለመግባትና ጉዳት የደረሰባቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች እንዲያገግሙ ማገዝ ነው:: እናም መገናኛ ብዙኃን የሰላም ስምምነቱ ወደ መሬት ወርዶ ሕዝቡ ተጠቃሚ እንዲሆን በኃላፊነት መንቀሳቀስ አለባቸው:: ስምምነቱን ከአውዱ ውጪ ባለመተርጎምና አገሪቱ ላይ የነበረው ነባራዊ ሁኔታ እንዲቀየር የሚያግዝ ሥራ ላይ ማተኮር ያስፈልጋቸዋል::

እያንዳንዱ የመገናኛ ብዙኃን ተቋም የተጎዱት እንዲበረቱና የማኅበረሰቡ የእርስ በእርስ መስተጋብር እንዲጠናከር በማድረግ የሰላም ስምምነቱ ከግብ እንዲደርስ አዎንታዊ ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል:: በዚህ ደግሞ ነገ ተስፋ የምናደርጋትን ኢትዮጵያ በሩቅ ሳይሆን በቅርብ እንድናያት እንሆናለን:: በተለያዩ ጊዜያት ውስጣዊ እና ውጫዊ ጫናዎችን እንዳታስተናግድም እናግዛታለን::

እስከዛሬ በነበረው ነገር ተሳስተናልም ብዙ ተፈትነናልም:: እናም በዚህ ይብቃ ማለት መጀመር የአሁን ሥራችን መሆን አለበት:: ይህን ጫና ለመቀልበስም መንግስትና መገናኛ ብዙኃን የጋራ መግባባት ፈጥረው ሊሰሩ ይገባል:: ለሀገራዊ አንድነት ከእነርሱ በላይ ማንም ስለሌለም የመገናኛ ብዙሃን ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃዎችን ከሚመለከታቸው አካላት በመቀበል ለህብረተሰቡ ማድረስም ያስፈልጋል::

Website - www.press.et Email - addiszemen@press.et Facebook - Ethiopian Press Agency

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

## ራሳችንን ከዘመን እድፍ፤ ከስልጣኔ ነውር መጠበቅ አለብን!

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

ፈረንጆች አሁን ያለንበትን 21ኛውን ክፍለ ዘመን የስልጣኔ ጥግ ይሉታል ... አንዳንዶች ደግሞ የዓለም ፍጻሜ ዋዜማ ያደርጉታል:: ሁለቱም እሳቤ አሁን ያለችውን ዥንጉርጉር ዓለም ይገልጻታል ብዬ አስባለሁ:: የእኔና የእናንተ አሁናዊ መልክ እንኳን ከዚህ የዘመን እድፍ ጋር የተለወሰ ነው:: ዘመን የበረከቱን ያክል የሚነጥቀን ብዙ ነገር አለው:: ጊዜ የእድሉን ያክል የሚቀማንና የሚወስድብን ብዙ ማንነት አለው::

ስልጣኔ ጌጥ ብቻ አይደለም፤ ነውርም፣ ኩነኔም ነው:: አረማመድ ካላወቅን፣ አያያዝ ካልቻልን ራሳችንን፣ ታሪካችንን ሊበርዝ የሚችል በርካታ ስውር ገጽ አለው:: የ21ኛው ክፍለ ዘመን እሳቤ በፈጠረውና ግሎባላይዜሽን በሚል ትስስር የተፈበረከው ዓለምን ወደ አንድ መንደር የማምጣት እሳቤ በረከቱ እንዳለ ሆኖ እኛን ከራሳችንና ሌላውንም ከራሱ ነጥቆታል ብዬ አስባለሁ:: አለምን አንድ ቦታ ላይ የማየት አባዜ በፈጠረው የስልጣኔ ልክፍት ምክንያት ተያይዞ በመጣው የዘመን አብዮት ተጽዕኖ ስር የወደቀ በርካታ ማንነት አለ::

ሰው ከዘመን ሲልቅ እንጂ ዘመን ከሰውነት ሲልቅ ውበት የለውም:: ዘመን ከሰውነት ሲልቅ የሚነጥቀን ብዙ ነገር አለው:: ዛሬ ላይ በስልጣኔ ስም ያጣናቸውና እያጣናቸው ያሉ ታሪኮቻችንና ማንነቶቻችን በዘመን መበለጣችን የፈጠረው ጣጣ ነው:: አንዳንዶች ዘመንን በልጠው፣ ከጊዜ ቀድመው ራሳቸውን ሳያስነኩ፣ ታሪካቸውን ሳያጎድሉ በኩራት ይኖራሉ:: ሰው በዘመን ሲበለጥና ዘመንን ሲበልጥ አንድ አይነት አይደለም::

የጠፉ ማንነቶች፣ የተበረዙ ታሪኮች በዘመን የመበለጣችን ምልክቶች ናቸው:: ሰው በጊዜ ሲበለጥ ምንም ነው... የዘመን ባሪያ፣ የጊዜ ሎሌ ከመሆን ያለፈ ጥቅም አይሰጥም:: ይሄ ዘመን ራሳችንን በንቃት የምንጠብቅበት ዘመን ነው:: ሁሉም ስልጣኔ ሊባርከን ወደ እኛ አልመጣም:: የዓለም ስርዐት ሰጥቶ የመቀበል መርህ ነው:: አንድ ስልጣኔ ወደ እኛ ሲመጣ የሆነ ነገራችንን ሊወስድብን ነው:: በጥንቃቄና በማስተዋል ዘመኑን መዋጀት ይኖርብናል::

የምንጠቀማቸው ስማርት ስልኮች፣ የምናያቸው ፊልሞች፣ የምንጫወታቸው ጌሞች የሚሰጡን ተዝናኖት እንዳለ ሆኖ ከጊዜ አኳያ የሚቀሙን ብዙ ነገሮች አሉ:: ጊዜን በንቃትና በብልጠት መቅደም አለብን:: ብዙ ጊዜያችንን ስልካችን ላይ ስናሳልፍ በጊዜ እየተበለጥን ነው:: ብዙ ጊዜያችንን ፌስቡክና ሌሎች ማህበራዊ መገልገያዎች ላይ ስናጠፋ በጊዜ እየተሸነፍን ነው::

ጊዜን የምናሸንፈው የሰጠንን በረከት በእውቀትና በምክንያታዊነት ስንጠቀመው ነው:: ለበጎ ነገር ስንገለገልበት ነው:: ዘመን የሰጠንን በረከት እንዴት፣ ለምን፣ መቼና የት እንደምንጠቀመው ካላወቅን እየጠፋን ነው:: ሰው ራሱን ካጣ ምንም ነው:: በህይወት ውስጥ እንዳናጣው ልንታገልለት የሚገባን አንድ እውነት ራሳችን ነው:: ራሳችንን ያጣን ቀን ሁሉም ነገራችን ይቆማል::

ሰጥቶ የመቀበል መርህ በሚገባ ካልተረዳነው አደገኛ መርህ ነው:: ስልጣኔ ምናችንን እንደሚወስድብን አናውቅም:: አንድ ቀን፣ ድንገት ራሳችንን አንሰንና ጎድለን እናገኘዋለን:: ‹‹ውሀ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው›› እንደሚባለው፣ እያዝናና እያጫወተ ልናስተካክለው ወደማንችለው የህይወት ቀውስ ይከተናል:: ስልጣኔ ህይወትን በብዙ መንገድ ያቀልልናል:: በዚያው ልክ የሰውን ልጅ ከህይወት ሙላት የማጉደል አቅምም አለው:: ምናችንን እንደሚወስድብን አናውቅም::

ካልነቃን ህልማችንን ሊወስድብን ይችላል:: አስተዋይ ካልሆንን ታሪካችንን፣ ማንነታችንን፣ ባህልና ወጋችንን አንድም ሳይቀር ሊበርዝብን ይችላል:: ዘመን የሰጠን የሆነ ነገር ላይ ብዙ ጊዜያችንን ስናሳልፍ ህልማችንን እያጣን፣ እቅዳችንን እየሳትን ነው ማለት ነው:: ልንሰራው የሚገባንን እንዳንሰራ ጊዜያችንን በመሻማት ከእቅዳችን እንድንዘገይ በማድረግ ወደ ኋላ ያስቀረናል::

> **ዘመኑ የስልጣኔና የስይጥንና ነው:: በርካታ የተሳሳቱና ሀገር አፍራሽ የሆኑ መልዕክቶች የሚነገሩበት:: ስልጣኔው ተራቅቆ በኮምፒዩተሩ ቁልፍ ማንም ቤቱ ሆኖ የፈለገውን የሚጽፍበት፣ የፈለገውን የሚዋሽበት ጊዜ ነው:: ሀገራችን በምክንያት የሚኖር፣ ስለሀገሩ የሚቆረቆር፣ እውነትን፣ እውቀትንና በጎነትን የተላበሰ ትውልድ ትሻለች**

ሁሉም ነገር ስርዐት አለው:: ሁሉም ነገር ልክና እውነት የሚሆነው በስርዐት ውስጥ ሲከወን ነው:: ጊዜ የሰጠንን በረከት በአግባቡ መጠቀም ከህይወት ሙላት እንዳንጎድል ያደርገናል የሚለው የዚህ ጽሁፍ ትልቁ መልዕክቴ ነው:: ህይወት ዘልማድ አይደለችም፤ እቅድና ተልዕኮ ናት:: በእያንዳንዱ እንቅስቃሴያችን ውስጥ የምናደርገው ነገርና የምንሆነው መሆን የህይወታችንን የወደፊት እጣ ፈንታ ይወስነዋል::

በእቅድና በመላ መኖር የዘመናዊነት አንዱ መገለጫ ከመሆኑም በተጨማሪ ለህይወት እሴት የሚጨምር ልምድ ነው እላለሁ:: ከተፈጥሮ መጉደል መሸነፍ ነው:: በዙሪያችን ያሉ ማናቸውም ነገሮች ከተፈጥሮ እንዳያጎድሉን እድል ልንሰጣቸው አይገባም:: በአሁኑ ወቅት ለወጣቱ አደገኛ ከሆኑ ሱሶች ውስጥ አንዱ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ነው::

እንዴት መጠቀም እንዳለብን ብቻ ሳይሆን ምን እየተጠቀምን እንደሆነ ካላወቅንም አደጋ ውስጥ ነን:: አጠቃቀማችን ጊዜያችንን ይወስነዋል:: ምን እየተጠቀምን እንደሆነ ማወቃችን ደግሞ ማንነታችንን ይታደገዋል:: እንዴትና ምን እየተጠቀምን እንደሆነ በማወቅ ጊዜያችንን ከመባከን፣ ራሳችንንም ከመጥፋት ልንታደገው እንችላለን::

በዘመን ስጦታ ከራሳችንና ከታሪካችን ከእውነትና ከተፈጥሮ ጎድለን ሌላ ሆነን እየኖርን ያለንበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው:: ሀገር፣ ትውልድና ማህበረሰብ መልካቸው እስኪጠፋን ድረስ ከማንነታችን ጎድለን እየኖርን ነው:: ባህል፣ ታሪክ ስልጣኔ ውሀ ሳያነሱ ዘመን አመጣሽ በሆነው አውሮፓዊ ስልጣኔ እየተወሰድን ‹‹ማን ናችሁ?›› ስንባል ማንነታችን እየጠፋን የተቸገርንበት ወቅት ላይ እንገኛለን::

እኔና እናንተ በዚህ ዘመን ለሚፈበረኩ ማናቸውም የውሸት ፈጠራዎች የተጽዕኖ ማረፊያ ነን:: ራሳችንን ከዘመን እድፍና ከስልጣኔ ነውር መጠበቅ አለብን:: ራሳችንን መከላከል ካልቻልንና የሰማነውና ያየነው ሁሉ ልክ እንደሆነ የምንቀበል ከሆነ የሌሎች መጠቀሚያ ከመሆን ባለፈ ለራሳችንም ሆነ ለሀገራችን የምናመጣው ትርፍ የለም:: ከሁሉም በፊት የስልጣኔን ትርጉምና ምንነት ማወቅ ይኖርብናል:: ስልጣኔ ራስን ከመውደድና ከመንከባከብ የሚጀምር ነው::

ስልጣኔ ራስን መተው፣ ራስን መርሳት፣ ማንነትን መቀየር አይደለም:: ስልጣኔ ትላንትን መናቅና የኋላን መተው አይደለም:: ስልጣኔ አስተሳሰብን መቀየር ነው:: ስልጣኔ መሰረትና መረጃ ከሌለው የህይወት ልማድ ተላቆ ወደ ላቀ እውነት መሸጋገር ነው:: አርነት የሚያወጣን እውነትና እውቀት እንጂ ሌላ ነገር አይደለም:: በእውቀት መኖር ደግሞ የዚህ ዘመን አንዱ የስልጣኔ መገለጫ ነው:: ያየነውን ሁሉ ማመን፣ የሰማነውን ሁሉ እንዳለ መቀበል ሳይሆን እውነቱ የቱ ጋ እንዳለ መመርመር ያስፈልጋል::

ይህ ዘመን ዓለም በእውቀት በስልጣኔ እንዲሁም በውሸትና በማስመሰል ጥግ የደረሰችበት ዘመን ነው:: በስልካችን እንኳን ብዙ ውሸቶችን የመቀበልና ብዙ ውሸቶችን የመላክ እድል አለን:: ዘመኑ ዘመናዊ ውሸቶች እንደ አሸን የፈሉበት ዘመነ ፍዳ ልንለው እንችላለን:: እውነቱ ውሸት፣ ውሸቱ ደግሞ እውነት የሆነበት ግራ የሚያጋባ ስልጣኔ ላይ ነን:: እንደወጣት እንደ አንድ ምርጥ ዜጋ የሰጡንን ሁሉ መቀበል ሳይሆን ‹‹ለምን?›› ብለን መጠየቅ ይኖርብናል::

እስከዛሬ እውነት የሚመስሉ፣ ለእውነት የቀረቡ ፍጹም ውሸቶችን ስንሰማ ኖረናል:: እኛም የፈጠርናቸው ሆኑ በሌሎች የተፈጠሩ ውሸቶች በማህበረሰቡ ላይ ይሄ ነው የማይባል ጥቁር ጠባሳዎችን አሳርፈው አልፈዋል:: ዘመናዊነታችንን ከእውነት እንጀምር:: ስልጣኔን ሀገርን ከመውደድና ሀገርን ከመጠበቅ እንጀምር:: ውሸት እውቀት አይጠይቅም፤ማንም ሊያደርገው የሚችል ነገር ነው::

የላቀው እውቀት በእውነት መኖርና በእውነት ሌሎች እንዲኖሩ መፍቀድ ነው:: ሀገራችን ከመቼውም ጊዜ በላይ እውነት ትሻለች:: በምንጠቀመው ማህበራዊ ሚዲያ ከቻልን ህዝብ የሚጠቅም፣ ትውልድ የሚቀርጽ አስተማሪ መልዕክት እንጻፍ..እናብብ:: ካልቻልን ደግሞ ዝም እንበል:: ዝምታ ውበት ነው:: ከክፉዎች ጋር አለመተባበርና የክፉዎችን ሀሳብ አለማስተጋባትም አንዱ የዘመናዊነት መገለጫ ነው::

እጆቻችንንና ኮምፒዩተሮቻችንን ለክፋት አንጠቀም:: እስከዛሬ ድረስ በኮምፒዩተር የታገዙ በርካታ ዘመናዊ ውሸቶችን ሰምተናል:: እነዚህ ውሸቶች እኛ ዘንድ ደርሰው የፈጠሩት ማህበራዊ ቀውስ አለ:: ራስን በእውቀትና በጥበብ በማነጽ ለሀገር ባለውለታ መሆን ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል:: እውቀት በምክንያት እንጂ በወሬ አይመራም...እውነት በተግባር እንጂ በይሆናል አይወሰንም::

ወሬኞች ስራቸው ማውራት ብቻ ነው... ሌላ ነገር ስለማይችሉ የተሻለ ነገር መፍጠር አይሆንላቸውም:: እኛ ደግሞ በእውነትና በእውቀት የውሸታሞችን ሴራ ተረት ማድረግ ይጠበቅብናል:: ስልጣኔ የሰው ልጅ የእውቀትና የማስተዋል ውጤት ነው:: የሰው ልጅ እውቀቱን ላልተፈለገ አገልግሎት ሲጠቀምበት ግን ስልጣኔ ስይጥንና ይሆናል::

ዘመኑ የስልጣኔና የስይጥንና ነው:: በርካታ የተሳሳቱና ሀገር አፍራሽ የሆኑ መልዕክቶች የሚነገሩበት:: ስልጣኔው ተራቅቆ በኮምፒዩተሩ ቁልፍ ማንም ቤቱ ሆኖ የፈለገውን የሚጽፍበት፣ የፈለገውን የሚዋሽበት ጊዜ ነው:: ሀገራችን በምክንያት የሚኖር፣ ስለሀገሩ የሚቆረቆር፣ እውነትን፣ እውቀትንና በጎነትን የተላበሰ ትውልድ ትሻለች:: እነዚህ የዘመናዊነት ጸዳሎች የዚህ ትውልድ መገለጫዎች ሊሆኑ ይገባል:: ሌላው ሁሉ የሚጥለን ነው:: ሌላው ሁሉ የሚያጎሳቁለንና ከክብራችን ዝቅ የሚያደርግ ነው::

ስልጣኔና ስይጥንና፣ እውነትና ማስመሰል የአሁኗ አለም አሁናዊ ስቃዮች ሆነው በየቤታችን አሉ:: አንዳንዱ የዘመኑን ጥሩ ነገር ተጠቅሞ ሀገር ይለውጣል፤ አንዳንዱ ደግሞ ስልጣኔውን ባልተፈለገ መንገድ በመጠቀም በውሸት ወሬ የግል አጀንዳውን ያራምዳል:: ማህበረሰባችን የወሬን አደገኝነት ሲገልጽ ‹‹ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው›› ይላል:: ወሬ ምን ያክል አደገኛ እንደሆነ ይህን አባባል መገንዘብ በቂ ነው::

እኛ ኢትዮጵያውያን ለወሬ ብርቅ አይደለንም:: ለበርካታ ዘመን በወሬና በአሉባልታ ፍቅራችንን፣ አንድነታችንን አጥተን እናውቃለን:: በውሸትና በማጭበርበር አብሮነታችንን፣ ኢትዮጵያዊነታችንን ተነጥቀን እናውቃለን:: ለዚህም እኮ ነው ‹‹ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው›› ብለን የተቀኘነው::

አሁንም ከውሸትና ከአሉባልታ አልወጣንም:: የሚጠቅመን ወሬ ሳይሆን ስራ፣ አሉባልታ ሳይሆን በጠረጴዛ ዙሪያ መነጋገር ነው:: እንደ ዜጋ፣ እንደወጣት የጊዜ አጠቃቀማችንን ማስተካከል አለብን:: በተለይ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ያለን አቋም ሊስተካከል ይገባል:: ጥሩ ነገር ምንና የት እንደተቀመጠ በመረዳት ሀገራችን አሁን ካለችበት ፈተና እንድትወጣ ማገዝ ይጠበቅብናል::

ወጣትነታችን ለሀገር የምንሰራበት፣ ህልማችንን የምናሳካበት እንጂ የማንም መጠቀሚያ የምሆንበት አይደለም:: በወጣትነታችን ውስጥ ሀገራችንን እንፈልጋት:: ስልጣኔ ለሀገር ከመስራት፣ ለሀገር ከማሰብ፣ ለሀገር ከመሞት የሚጀምር ነው:: ለሀገር ስንሰራ ለራሳችንና ከእኛ በኋላ ለሚመጣውም ትውልድ እየሰራን ነው:: ስልጣኔያችንን ከሀገር እንጀምር:: ሀገር በመውደድ፣ የራስን እውነት ከመቀበል እንጀምር::

ባህልና ታሪክን በማክበር ወደምንፈልገው የስልጣኔ ጥግ መሄድ እንችላለን:: በጊዜ ከመበለጥ ይልቅ ጊዜን በመብለጥ ከፍ ማለት እንችላለን:: የዚህ ዘመን አብዛኛው ስልጣኔ ከራስ ሽሽት ነው:: ሀገርና ህዝብ፣ ታሪክና ባህል የሚለይ ነው:: ከወግ ባህል የሚጣረስ ነው:: እውነተኛ ስልጣኔ ደግሞ በትላንት እውነት ውስጥ ዛሬን መፈለግ እንጂ ትላንትን ትቶ ወደ ነገ መሄድ አይደለም:: የኋለኛው ከሌለ የፊተኛው የለም፡፡ እውነተኛ ስልጣኔ በራስ እውነት ውስጥ መኖር ... በትላንት ዳና የዛሬን አብራክ መፈለግ ነው::

# የ’ርስ በርስ ግጭቶቻችን መፍቻዎቻችን

ግርማ መንግሥቴ

ግጭት የትም አለ። ከአባባላችን ጀምሮ ”እንኳን ሰውና ሰው፣ እግርና እግርም ይጋጫል” ይባላል። ችግሩ ያለው፣ የተፈጠረውን ግጭት ማስተናገዱ ላይ ነውና ወደ’ዛው እንሂድ።

”ኢትዮጵያ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን ከዘመናዊው ሕግ ጋር አብራ እንድታስኬድ የሰላም አባቶች መከሩ።” የሚል ዜና ከመገናኛ ብዙኃን (ለምሳሌ፣ ኢዜአ፤ ጥር 5/2012 ዓ.ም) መስማታችን ለብዙዎቻችን እንግዳ አይደለም። ጋሞ ጎፋ ዞን (ጋሞ ብሄረሰብ) ከቤተሰብ ጀምሮ ለሚፈጠር ጸብ የራሱ የሆነ ባህላዊ የግጭት አፈታት (በቤተሰብ ውስጥ የሚፈጠር ጸብ የሚፈታበት “ኡሩሻ” የተሰኘ የእርቅ) ስርአት አለው። ይህ ደግሞ በተግባርም የታየና አገርና ሀብትን ያዳነ ስለ ሆነ ብዙ መነጋገር ወይም ማብራሪያ የሚያስፈልገው ጉዳይ አይደለም።

በዞኑ ወይም በብሄረሰቡ ከቤተሰብ፣ ከፍ ሲልም ሰዎች ወደ ግጭት እየገቡ አይቶ ማለፍ በአካባቢው አጠራር “ጎሜ” ወይንም ሃጢያት በመሆኑ የተወገዘ ነው። ተጋጭተው ከተገኙም፣ በተጋጪዎች መካከል ገብቶ ለምለም ሳር፣ ኩታ ወይንም ጋቢ፣ የእንስሳት ቆዳና ሌሎች የጸብ ማብረጃ ተብለው የሚታወቁትን በመያዝ ፀቡ እንዲበርድ ይደረጋል።

በባህሉ መሰረት ጸብን ለማብረድ እድሜ የማይጠይቅ ሲሆን፤ ተጋጭዎች ወደ ግጭት ሊያመሩ የነበሩ ግለሰቦች ተረጋግተው “ዱቡሻ” ወደ ተሰኘ የግጭት አፈታት ስርአት በመሄድ ሰላምና እርቅ እንዲወርድ ይደረጋል። ግጭት ወደ ሁከት ከማምራቱ በፊት የመከላከል ተግባር በዱብሻ የተሰየሙ አባቶች ተግባር ሲሆን፤ በስርአቱ የሰውን ንብረት መዝረፍ፣ አስገድዶ መድፈር፣ ሰውን መግድል፣ ጸብ ማጫር የተወገዘ ነው። ከላይ በጠቀስነው ቀን ከኢዜአ ጋር ቆይታ ያደረጉት በአሁኑ ወቅትም የጋሞ የሰላም አባት በመሆን በዱቡሻ የእርቅ ስርአት ውስጥ እያገለገሉና ከአባቶች የወረሱትን ባህል ለአዲሱ ትውልድ እያስተማሩ የሚገኙት የእድሜ ባለጸጋው አቶ ዘለቀ አርጃሞ ከልጅነታቸው ጀምሮ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በዚህ ባህላዊ የእርቅ ስርአት መፍታት እንጂ ወደ ዘመናዊ ሕግ ተቋማት ሄደው እንደማያቁ ተናግረዋል።

‹‹የጋሞ ሽማግሌዎችም ሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያዊያን እንደየአካባቢው ባህልና ወግ መሰል የግጭት አፈታት ዘዴዎች ያላቸው በመሆኑ መንግስት ከዘመናዊ የህግ ስርአት ጋር በማዋሃድ ቢተገብረው የሚፈጠሩ ችግሮችን ከጅምሩ መፍታት ይቻላል የሚል እምነት አላቸው።” የሚል አስተያየትን የሚሰነዝሩት ከዚህ አይነቱ ቱባ እሴት በመነሳት መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል።

የዞኑ ቱሪዝምና ስፖርት መምሪያ ሃላፊ አቶ ዘነበ በየነም ”የጋሞ ባህላዊ የእርቅ ስርአት በአካባቢው ጸብን የማብረድ ሚናው የጎላ ነው” በማለት ነው የአቶ ተስፋዬን አስተያየት የሚያፀኑት። ባህሉን ለሌሎች አካባቢዎችና ለአዲሱ ትውልድ ለማስተዋወቅ የህትመትና የተለያዩ መገናኛ ዘዴዎችን እየተጠቀሙ መሆኑንና ሌሎችም ይህንኑ ልምድ እንዲጠቀሙ መክረዋል።

ኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች ከራሷ አልፋ ለሌሎች የአፍሪካ አገሮች ሰላምን ለማውረድ የሚጠቅሙ በርካታ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች አሏት። በመሆኑም ይህ የሚመለከታቸው አካላት ህግ አውጪዎችን ጨምሮ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአት እንዲዳብር እንዲሁም ከዘመናዊ የህግ ስርአት ጋር እንዲቀናጅ ማድረግ ላይ መስራት አለባቸው።

ኢትዮጵያ የተለያዩ የግጭት አፈታት ብልሀቶች ያሏትና ህብረትን፣ አንድነትን፣ ወንድማማችነትን፣ መቀራረብን የሚሰብኩ እሴቶች ባለቤት ሆና ግጭት ሊበረታባት እንደማይገባ በቁጭት የተናገሩት አቶ ተስፋዬ (በ2011 ዓ.ም በአርባ ምንጭ ሊከሰት የነበረውን ግጭት እንዲረግብ ካደረጉ የጋሞ የሰላም አባቶች መካከል አንዱ)፤ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ካላቸው ተቀባይነት አንጻር እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን የመቀነስ አቅም አላቸው። በመሆኑም፣ በእነዚህ ባህላዊ የግጭት አፈታትና ባህላዊ እሴቶች ውስጥ ያደገ ወጣት የአባቶችን ምክር እንዲሰማ ጠይቀው መንግስትም እሴቱን እንዲጠቀምበት ይመክራሉ።

ወደ ጉራጌ እንሂድ። የሪፖርተሩ ሲሳይ ዓለሙ ”የጉራጌዎች ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥነ ሥርዓት” በሚል ርእስ ለንባብ አብቅተውት በነበረ ጽሑፍ



ላይ አንድን አዛውንት ”ድሮ እናንተ እንደኛ ወጣት በነበራችሁ ጊዜ አሁን በአገራችን እንደተከሰተው ዓይነት ምክንያቱ እንኳን ይህ ነው በማይባል ፀብ፣ ክርክር፣ ዘረኝነት፣ ግድያ ነበረ እንዴ? ብዬ ጠየቅኳቸው።” ይላሉ። ቀጥለውም ‹‹ሰው ለሰው ይቅርና እግርና እግር ይጋጭ የለም፣ ፀብማ ነበረ’ አሉኝ። ’ግን እውነት እልሃለሁ ልጄ እንደ አሁኑ ዓይነት የዘር፣ የብሔርና የጎሳ ግጭት ግን ዓይቼም፤ ሰምቼም አላውቅም። [...] ልጄ አንዴ ሆኗል፤ እናንተ ወጣቶች በየአካባቢያችሁ ያለውን የግጭት አፈታትና የዕርቅ ሥነስርዓት ላይ አተኩራችሁ ልትሠሩ ይገባል። አገራችሁን ኢትዮጵያ ጠብቋት’ ብለውኝ በነበርኩበት ጥለውኝ ሄዱ።” በማለት አስነብበው ነበር።

ይህንን እዚህ መጥቀሳችን ብዙ ነገርን የተሸከመ ሀሳብ ስለቀረበበት ነው። ዘመንም አንዱ በዚሁ እቅፍ ውስጥ የሚገኝ ፅንሰ ሀሳብ ነው። ጸሐፊው ”ጉራጌዎች እያንዳንዱ ተግባራቸው፣ ወግና ልማዳቸው፣ ሐዘንም ደስታቸው፣ የግጭት አፈታታቸው፣ የአረማመድና የአበላል ሥነ ሥርዓታቸው የጉራጌ ሽማግሌዎች ተሰባስበው አርቅቀው፣ ቃለ መሃላ በፈጸሙባቸው የጆካ ቂጫ፣ ሴራና የጎርደነ ባህላዊ መተዳደሪያቸው ላይ ባስቀመጡት ሕግና ደንብ መሠረት ነው የሚመሩት። መላው ቤተ ጉራጌ የእነዚህ ደንብና ሕጎች ያለማቅማማት ተገዥ ነው።” በማለት ያሰፈሩትም ለጥቅስ የሚበቃ ብቻ ሳይሆን አስተማሪም ነውና እዚህ ሊጠቀስ የግድ ይሆናል።

ጸሐፊ ”ጥሉን የፈጠሩ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች ጉዳያቸውን በቀነ ቀጠሮው መሠረት ሽማግሌዎቹ በዝርዝር ተመልክተው እስኪፈቱት ድረስ በመሃል ምንም ዓይነት የጥላቻ ንግግር እንዳያካሄዱ፣ ጥልም ሆነ ግጭት እንዳያስነሱ ሽማግሌዎቹ ከበድ ካለ ማስጠንቀቂያ ጋር ‹‹ኸተራት›› ይሰጣሉ።” ካሉን በኋላም ”ኸተራት ማለት ጉዳዩን በሽማግሌዎች እስኪታይ ድረስ በመሀል ምንም ዓይነት ጥልም ሆነ ዘለፋ እንዳይካሄድ የሚደነግግ ባህላዊ ሕግ ነው። ይህን ኸተራት የጣሰ አካል ከፍተኛ የሆነ ቅጣት ይወሰንበታል። ቅጣቱ ከማንኛውም ዓይነት የማኅበራዊ ጉዳዮች እስከ ማገድና ማግለል ሊደርስ ይችላል። ለዚህም ነው ጉራጌዎች ለኸተራት ልዩ ሥፍራ የሚሰጡት።” በማለት የጉራጌን ባህላዊ ግጭት አፈታት ዘመናዊነት ይነግሩናል።

ውሳኔ አሰጣጥን በተመለከተም ”ሽማግሌዎቹ የጥፋት ብይኑን ለማስተላለፍ እውነት እንደ ፀሐይ ትብራ፤ እንደ ጨረቃም ትድመቅ በማለት የመከፈቻ ንግግራቸውን ካካሄዱ በኋላ ጥፋቱን ማን ጋር እንደሆነ በአንድ ድምፅ ይወስናሉ። ለደቂቃዎች ከቦታው ገለል እንዲሉ የተደረጉ ባለጉዳዮች እንዲቀርቡ ከተደረገ በኋላ ከታላቅ ተግሳጽና ምክር ጋር ለአጥፊው ወገን የጥፋቱን ሁኔታ በዝርዝር በተመደቡ ሽማግሌዎች አማካይነት ይነገረዋል።

በውሳኔው አጥፊው ወገን ቅሬታም ሆነ አስተያየት እንዲያቀርብ ዕድል ይመቻችለታል። ያቀረበው ቅሬታ አሳማኝ ከሆነ ጉዳዩን በድጋሚ እንዲታይለት ይደረጋል። ካልሆነም ደግሞ አጥፊው ወገን ዳግም እንደዚህ ዓይነት ጥል ያላግባብ በሠፈሩና ከማንኛውም ዓይነት ግለሰብ ጋር እንዳይፈጠር ከማስጠንቀቂያ ጋር ቅጣቱን እንዲከፍል ይደረጋል። እንደየ ሁኔታው ሽማግሌዎቹ የቅጣት ማቅለያ ካለ ያደርጋሉ። በቅጣት የሚገኝ ገንዘብም ሆነ ማንኛውንም ዓይነት ንብረት ሽማግሌዎቹ በሚወስኑት ውሳኔ መሠረት ዕድራቸው ወይም የጋራ በሆኑ የማኅበራዊ ጉዳዮቻቸው ላይ እንዲውል ይደረጋል።” ሲሉ በጉራጌ ባህላዊ-ዘመናዊነት ላይ እንድንደመም ያደርጉናልና እናመሰግናቸዋለን።

”በማንኛውም ዓይነት፣ በጥልም ሆነ ባለመግባባት ወቅት የሰው ነፍስ ከጠፋ ጉራጌዎች እስከ ሰባት ዓመት የሚውስድ ባህላዊ የዕርቅ ሥነሥርዓት አላቸው።” ሲሉም ፅሁፋቸውን ይደመድማሉ። (ሌሎችንም በተመለከተ አብዱልፈታህ አብደላ ያዘጋጁትን፣ ”የኢትዮጵያ የሀገር በቀል የአስተዳደር፣ የህግና የፍትህ ሥርአቶች ማውጫ፤ ቅፅ 1”ን መመልከት ይቻላል። በተለይም በ”ክፍል አራት” ስር የሚገኘውን ”በደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚገኙ ...” በሚል ርእስ ስር የተካተተውን ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል።) ሌላውና ባህላዊ እሴቱ ወደ ሆነው "አፊኒ" እናምራ።

ባለሙያዎቹ ”ሀገር በቀል ዕውቀቶች ለዘመነው ማኅበረሰብ ምሰሶዎች ናቸው።” እንደሚሉት ሁሉ፣ የአማርኛ ትርጉሙ "ሰማችሁ ወይ" ማለት የሆነው "አፊኒ" የሲዳማ ህዝብ እንደማኅበረሰብና እንደ ትውልድ ለዘመናት ጠብቆና ተንከባክቦ ያቆየው የራሱ የሆነ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ነው። የፎክሎር (የባህል ጥናት) ባለሙያው ሙሉነህ ካሳ የአካባቢው ተወላጅ አዛውንት የሆኑትን አቶ መብራቱ ማቲዎስ አፊኒን ጠቅሶ እንደሚነግረን ከሆነ በሲዳማ ባህል ሰዎች ሲናገሩ "አፊኒ" ሳይባል ጣልቃ አይገባም። በሌላ መልኩ አንድ የተበደለ ሰው ማንኛውም አይነት እርምጃ ከመወሰዱ በፊት በአጠገቡ ላሉት ወይም ለታላላቆቹ "አፊኒ" በማለት ማሳወቅ ባህላዊ ግዴታው ነው። ይህንን ሳያደርግ በግብታዊነት እርምጃ የወሰደ እንደሆነ ቅጣት ይጣልበታል። አጥፊው ቅጣቱ በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት እንዲያጣ ስለሚያደርገው ከባድ ይሆንበታል። ከቅጣቶቹ ውስጥ እድር፣ እቁብ ወይም ሌሎች ማኅበራዊ ተሳትፎዎች ላይ ያለውን ሥልጣንና መብት እንዲያጣ፣ እንዳይሸጥ እና እንዳይገበይ፣ ልጆቹን እንዳይድር የሚከለክሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

አፊኒ እውነትን ከማፈላለግና ከፍትሕ አሰጣጥ ጋር በእጅጉ ይተሳሰራል። እውነትን በማጣራትና በማረጋገጥ ወደ’ሚቀጥለው እርምጃ ለመራመድ አፊኒ ወሳኝ መንገድ ነው። ይህም የሚሆነው አፊኒ በጉዳዩ ላይ እውቀት ያለው ማንኛውም ሰው መረጃ እንዲሰጥ ሰፊ እድል ስለሚሰጥ ነው። በመሬት፣ በድንበር፣ በትዳር፣ ነፍስ በማጥፋት፣ በጠለፋ፣ የሰው ሀቅ በመብላት፣... ስሞታ የቀረበባቸው ጉዳዮች ወደ ሕግ ከማምራታቸው በፊት በሲዳማ ባህል በአፊኒ ስርዓት ይዳኛሉ።

በማኅበረሰቡ ዘንድ ግጭቶች በአፊኒ የመፈታት እድላቸው ከፍ ያለ ነው። ... አፊኒ በአንድ እና በሁለት ሰዎች መካከል ውሳኔ አይሰጥም። አራት እና አምስት ከዚያም በላይ በሆኑ ሰዎች አማካኝነት ይከወናል። አፊኒ በጉዱማሌ (ጉዱማሌ ቀጥተኛ የአማርኛ ትርጉሙ “አደባባይ” ማለት ሲሆን፤ የፍቼ ጫምባላላንና የዳኝነት ስነ-ስርአትን ጨምሮ ሌሎችም ማኅበራዊ ጉዳዮች ይከናወኑበታል።) እና መሰል ትልቅ የዋርካ ጥላ የሚገኝባቸው የሸንጎ አውዶች ላይ ይከወን እንጂ በዕለት-ተእለት መስተጋብር ውስጥ ሰዎች ሲጋጩ እዚያው በተጋጩበት ቦታ ላይ አስታራቂዎች ደርሰው ቦታ ሳይመርጡ በአፊኒ ስርዓት መሰረት ግጭቱን ሊፈቱ ይችላሉ” ሲልም ያብራራልናል።

”በአፊኒ ስርዓት መሠረት ሽማግሌዎች ቁጭ ብለው "halaale" (“ሀላሌ” ሀገር በቀል እውቀትን በመመርኮዝ በሸንጎ አውዶች ላይ ጭምር እውነትን ይዞ በመቅረብ ሃቅን ለባለሀቁ የመፍረድ ሂደት ሲሆን፤ በሲዳማ ብሄር ዘንድ ፈጣሪ ነው ተብሎም ይታመናል። "hola halaale" የሚባል የሚታመን መርህም አላቸው። ይህም (እግዚኦ ለእውነት) እንደማለት ነው።”) ስራ ይሰራሉ።” ሲልም ያክላል።

የጌዴኦን ”ኦዳ ያዓ ሶንጎ” ባህላዊ ሸንጎንም ከዚሁ ጋር አያይዞ ማየት ይቻላል። በግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል ግጭት ቢፈጠር፤ ተጎጂው አካል አጠገቡ ላሉ ሰዎች አፊኒ (ሰማችሁ ወይ) መበደሌን ብሎ ስሞታውን ያሰማል። አፊኒ ከተባለ በኋላ ግጭት ይረግባል። ወቃሽ እና ተወቃሽን የመለየት እንዲሁም ችግሮችን የመፍታት ስራ ነው የሚሰራው። በየፍርድ ቤቱ ያሉ መጉላላቶችን፣ ጊዜ እና ወጪን ይቆጥባል፣ ማኅበራዊ ትስስርን ያጎለብታል። ትልልቅ ግጭቶች በሚኖሩበት ጊዜ በአፊኒ ውስጥ "ቆሬ" (ነገርን ለነገ ማሳደር ወይም ጉዳዩ ጀርባው ይጠና እንደማለት) የሚባል ስርአት አለ። ተበዳይን ”ሄደህ ከልጆችህ ከቤተዘመዶችህ መረጃ አሰባስበህ ቅረብ” የሚባልበት መሆኑን የእሴቱ ባለ ቤቶች ይናገራሉ።

“ለምሳሌ አንድ የሰውን ንብረት የሰረቀ ግለሰብ መስረቁን ሽማግሌዎች ተሰብስበው በሀላሌ መርህ መሰረት እንዲያምን ይጠየቃል። አላምን ካለ "hola halaale" (እግዚኦ ለእውነት) ብለው እውነቱን ለፈጣሪ ትተው ይለያያሉ። ይህም ሽማግሌዎቹ እውነታውን ለፈጣሪ በመተዋቸው የተበላው የሰው ሀቅ መቅሰፍትን ይዞ ይመጣል ተብሎ ይታመናል። ለዚህም ነው የሲዳማ ማኅበረሰብ መቅሰፍት ከመምጣቱ በፊት የሀላሌ መርህ ባህላዊ እሴትን የእለተ እለት የህይወት መስተጋብሩ ያደረገው” ሲልም የክልሉን ባህል፣ ቱሪዝም እና ስፖርት ኮምዩኒኬሽን ቢሮ ጠቅሶ ያብራራል።

”ለሲዳማ ከሀላሌ በላይ መሀላ የለም። ሀላሌ ከ“ማጋኖ” (ፈጣሪ) ጋር የሚያገናኝ ድልድይ” ነው። ”የሀላሌን መርህ የሚጥስ ማንኛውም የብሄረሰቡ ተወላጅ በራሱ ላይም ሆነ ከእርሱ በሚፈጠረው ተከታይ ትውልድ ላይ መልካም ነገር አይገጥመውም የሚል ፅኑ እምነት በማኅበረሰቡ ዘንድ አለ” ሲልም ሀሳቡን ያስረግጣል።

በባሌ ዞን የተደራጁ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ለህብረተሰቡ አማራጭ የፍትህ ተቋም ሆነው እያገለገሉ እንደሚገኙ፤ የዞኑ የባህላዊ ፍርድ ቤቶች የሶስት ወራት የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ በሮቤ ከተማ በህዳር 8 ቀን 2015 ውይይት መካሄዱ፤ በዞኑ ከ200 በሚበልጡ ቀበሌዎች የተደራጁት ባህላዊ ፍርድ ቤቶች በህብረተሰቡ መካከል የሚያጋጥሙ አለመግባባቶችን በቅርበት በመፍታት አማራጭ የፍትህ ተቋም ሆነው እያገለገሉ እንደሚገኙ ኢዜአ፣ ህዳር 9 ቀን 2015 ይዞት በወጣው ዜና አመላክቷል።

በዚሁ ሥራ ላይ ባህላዊ ፍርድቤቶቹ ተቋማቱ ህብረተሰቡ በማህበራዊ መስተጋብር የሚያገጥሙትን አለመግባባቶች ወደ መደበኛ ፍርድ ቤቶች በመውሰድ ያወጣ የነበረውን ገንዘብ፣ ጊዜና ጉልበት ለልማት ስራው እንዲያውል እያስቻሉት መሆናቸው ፤ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ላይ ይደርስ የነበረውን የሥራ ጫና በማቃለል ለፍትህ ስርዓቱ መሻሻልም የላቀ አስተዋጽኦ እያበረከቱ እንደሚገኙም ጠቅሷል።

ባህላዊ ፍርድ ቤቶቹ ባለፉት ሶስት ወራት ወደ መደበኛው ፍርድ ቤት ይመጡ የነበሩ ከ7ሺህ በላይ የክስ መዝገቦችን በሽምግልና መፍትሄ እንዲያኙ ማድረጋቸው፤ በህብረተሰቡ መካከልም መቀራረብን እያጎለበቱ እንደሆነ፤ እየተቀዛቀዘ የነበረውን አገር በቀል የግጭት አፈታት ስርዓት ተቋማዊ በሆነ መልኩ እንዲተገበር እድል መፍጠራቸውንም አውስቷል። (በኦሮሚያ ክልል ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች በተጨማሪ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች እንዲቋቋሙ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 240/2013 ጨፌ ኦሮሚያ በማጽደቅ ሥራ ማሥጀመሩ ይታወሳል።) ከዚህ ሁሉ የምንረዳው አቢይ ጉዳይ ቢኖር ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአቶቻችን ተጠናክረው መቀጠል፤ ተቋማዊ በሆነ መልኩም እንደገና መመስረት ያለባቸው መሆናቸውን ሲሆን፤ ይህንን ልምድ ሁሉም ክልሎች ሊወስዱት፤ ከገባንበትም አዘቅት እንወጣ ዘንድ ስራ ላይ ሊያውሉት ይገባል እንላለን።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## ዲጂታል ስራ ፈጠራ በወጣት ሴቶች

አስናቀ ፀጋዬ



ሚስተር አህመድ ተሃድሪ፤



ወጣት ዝማሬ ታደሰ፤



ወጣት ጁሊያና ቡሳሲ፤

ቴክ አፍሪካ ዉሜን (Tech Africa Women /TAW/) በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የሚደገፍ የስራ ፈጠራ ፕሮግራም ሲሆን ተቀማጭነቱን በቱኒዚያ ባደረገና ዲጂታል ቢዝነስ ግንባታ ላይ ትኩረቱን አድርጎ በሚሰራ ‹‹ቤትኪዩብ›› በተሰኘ ተቋም ይተገበራል:: የፕሮግራሙ ዋነኛ ዓላማም የአፍሪካ ወጣት ሴት ስራ ፈጣሪዎችን ማብቃትና በሴቶች የተመራ ጠንካራ የቴክኖሎጂ መነሻ ቢዝነስ መገንባት ነው::

የስራ ፈጠራ ፕሮግራሙ እ.ኤ.አ ከነሃሴ 2022 ጀምሮ ለአምስት ወራት ያህል ከኢትዮጵያ፣ ሴኔጋል፣ ታንዛኒያና ቱኒዚያ በተውጣጡ ወጣት ሴት የዲጂታል ቢዝነስ ሃሳብ አመንጪና ጀማሪዎች መካከል ሲከናወን ቆይቷል:: ከ331 አመልካቾች ውስጥ 74 የሚሆኑት ተመርጠው በካምፕ ሆነው አዲስ ለሚጀምሩት የዲጂታል ቢዝነስ ማጎልበቻ ጠቃሚ ግብአት የሚሆን የሶስት ቀን ስልጠና ተሰጥቷቸዋል:: የእርስ በእርስ ውድድር አካሂደውም አሸናፊ ቡድኖች ተመርጠው የ2 ሺ ዶላር ሽልማት አግኝተዋል::

ከ74ቱ ተወዳዳሪዎች ውስጥ ደግሞ ስምንቶቹ ተመርጠው ለአስራ ሁለት ሳምንት አዲስ የሚጀምሩትን የዲጂታል ቢዝነስ የኦን ላይን ትምህርቶችን በመውሰድ ሲያበለፅጉ ቆይተዋል::በመጨረሻም ከአራቱ አገራት ውስጥ የተመረጡት የመጨረሻዎቹ ስምንት ወጣት ሴት የዲጂታል ቢዝነስ መነሻ ስራ ፈጠራ ሃሳብ ባለቤቶች ስራዎቻቸውን አዲስ አበባ ላይ አቅርበው ከተወዳዳሪዎቹ ውስጥ ‹‹ኡጃና›› የተሰኘ የስነ ተዋልዶ ጤና ምርቶችንና የምክር አገልግሎቶችን ለወጣቶች የሚያቀርብ የኤሌክትሮኒክ ግብይት ፕላትፎርም በመፍጠር ታንዛኒያዊቷ ጁሊያና ቡሳሲ የ7 ሺ ዶላር አሸናፊ ሆናለች::

ለመጨረሻው ዙር ውድድር ሁለት ወጣት ሴት ኢትዮጵያውያን የዲጂታል ቢዝነስ መነሻ ስራ ፈጠራ ሃሳብ ይዘው በመቅረብ ብርቱ ፉክክር ቢያደርጉም ድል አልቀናቸውም:: ይሁንና የጀመሩትን የዲጂታል ቢዝነስ ስራ ፈጠራ ይበልጥ በማበልፀግ ገቢ ለማመንጨት ጠቃሚ ግብአቶችን ከፕሮግራሙ ማግኘት ችለዋል::

ጁሊያና ቡሳሲ በታዘንዛኒያ የህክምና ባለሞያና የህዝብ ስራ ፈጠራ ባለቤት ናት:: በቴክ አፍሪካ ዉሜን ስራ ፈጠራ ፕሮግራም ለመጨረሻው ውድድር ከቀረቡ ስምንት ተወዳዳሪዎች ውስጥ አንዷ ስትሆን ‹‹ኡጃና›› የተሰኘ የስነ ተዋልዶ ጤና ምርቶችንና የምክር አገልግሎቶችን ለወጣቶች የሚያቀርብ የኤሌክትሮኒክ ግብይት ፕላትፎርም /ቢዝነስ ሞዴል/ በመፍጠር የውድድሩ አሸናፊ ለመሆን በቅታለች:: በዚህም የ7 ሺ ዶላር ተሸላሚ ሆናለች::

ያገኘችው ሽልማት እንዳስደሰታት የምትገልፀው ወጣቷ፤ በቀጣይ ፕላትፎርሙን የመሞከር ስራ እንደምታከናውንና ጠቃሚ ግብአቶችን በመሰብሰብ የቢዝነስ ሞዴሉን ይበልጥ የማበልፀግ ስራ እንደምታከናውን ታስረዳለች::

በአፍሪካ ያሉ ማንኛውም ወጣት ሴቶች ሃሳብና ትልም እስካላቸው ድረስ ለማህበረሰቡ አውጥተው ለማጋራት መፍራትና ወደኋላ ማለት እንደማይገባቸውም ትገልፃለች::

እርሷም ይህን የፈጠራ ሃሳብ ካመነጨች ረጅም ግዜ እንደሆናት ተናግራ፤ ብርታቱን እስከታገኝ ድረስ ሃሰቡን ወደተግባር ለመለወጥ ስታመነታ መቆየቷን ታስረዳለች:: ነገር ግን ቴክ አፍሪካ ዉሜን የስራ ፈጠራ ፕሮግራም ሲጀመር የፈጠራ ሃሳቧን እውን የምታደርግበት አጋጣሚ መፈጠሩን ትናገራለች::

ፕሮግራሙም የፈጠራ ሃሳቧን ለመገንባትና ዲጂታል ቴክኖሎጂውን በመጠቀም የስነ ተዋልዶ ጤና ምርቶችንና አገልግሎቶችን በኤሌክትሮኒክስ ግብይት ፕላትፎርም አማካኝነት ለወጣቶች ለማቅረብ የሚያስችል የቢዝነስ ሞዴል ለመፍጠር እንዳስቻላት ታብራራለች:: ይህም በአጭር ግዜ ውስጥ ፍሬያማ ይሆናል ብላ እንዳላሰበች ትጠቅሳለች::

‹‹በሞያዬ ሃኪም ነኝ ነገር ግን በቴክኖሎጂ አማካኝነት ስራ ፈጣሪ መፍትሄ ማምጣት አልችልም ማለት አይደለም›› የምትለው ወጣት ጁሊያና የአፍሪካ ወጣት ሴቶች የቢዝነስ ሃሳብ እስካላቸው ድረስ በየትኛውም የሞያ መስክ ውስጥ ሆነው ቴክኖሎጂውን ተጠቅመው ስራ መፍጠርና በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ችግሮችን መፍታት እንደሚችሉ ትናገራለች:: ለዚህም ሃሳባቸውን ወደተግባር ሊለውጡ የሚያስችሏቸውን ማንኛውንም እድሎች መጠቀም እንዳለባቸው ትመክራለች::

ወጣት ዝማሬ ታደሰ በዚሁ በሞያዋ ሃኪም ስትሆን በዚሁ የስራ ፈጠራ ፕሮግራም ለመጨረሻው ውድድር ከቀረቡ ስምንት ምርጥ ተወዳዳሪዎች ውስጥ አንዷ ናት:: ‹‹ጤና ሰብ›› በተሰኘ መተግበሪያ አማካኝነት የፆታና የስነ-ተዋልዶ ትምህርትና የምክር አገልግሎት ለሴቶች የሚሰጥ የቢዝነስ ሞዴል ይዛ ነው ለውድድሩ የቀረበችው:: ይህን ፕላትፎርም ለማዘጋጀት ያነሳሳት ደግሞ ሴቶች የፆታና ስነተዋልዶ ጤና ትምህርትና የምክር አገልግሎት እንደልብ አለማግኘታቸው ነው::

በዚህ ቢዝነስ ሞዴል መሰረት ሴቶች ስልክ በመደወልና ድረገፅ በመጎብኘት የፆታና የስነተዋልዶ ጤና ትምህርትና የምክር አገልግሎት ያገኛሉ:: በሌሎች ማህበራዊ ሚዲያዎችም ሴቶቹ ትምህርቱንና የምክር አገልግሎቱን ለማግኘት ያስችላቸዋል::

በዚሁ መተግበሪያ አማካኝነት ትምህርቱንና የምክር አገልግሎቱን የሚፈልጉ ሴቶች ርቀት ሳይገድባቸው ካሉበት ቦታ ሆነው ይመዘገባሉ:: በተመሳሳይ በዚሁ ዘርፍ ሞያው ያላቸው የህክምና ባለሞያዎችም በመተግበሪያው ላይ ይመዘገባሉ:: በዚሁ መሰረት ሴቶቹ ወደ መተግበሪያው ገብተው የፈለጉትን የህክምና ባለሞያ በፆታ፣ በስፔሻሊቲና በህክምና ልምድ መርጠው ቀጠሮ ያሲዛሉ:: በቀጠሯቸው አማካኝነት ደግሞ ከመረጡት ሃኪም ጋር ተገናኝተው የትምህርትና የምክር አገልግሎቱን ያገኛሉ::

ሚስጥራቸውን ለመጠበቅ ደግሞ ስማቸው ሳይታወቅ ትምህርቱንና ምክር አገልግሎቱን የሚያገኙበት አሰራርም በዚሁ መተግበሪያ ላይ ተዘርግቷል:: ለሚያገኙት የፆታና የስነተዋልዶ ጤና ትምህርትና የምክር አገልግሎት ሴቶቹ ክፍያ ይከፍላሉ:: ከዚሁ ጎን ለጎን በርካታ ተከታዮች ባሉት የዚሁ ፕላትፎርም አንዱ አካል በሆነው ማህበራዊ ሚዲያ ላይ የተለያዩ ኩባንያዎች ምርታቸውን እንዲያስተዋውቁ በማድረግ ተጨማሪ ገቢ እዲገኝ ይደረጋል::

አገልግሎቱን ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ የቴሌኮም መሰረተ ልማት እንደልብ አለመስፋፋትና ፈጣን አለመሆኑን እንደ አንድ ችግር በመለየት ተጠቃሚዎች በስልክ ጥሪ አማካኝነት አገልግሎቱን የሚያገኙበት አሰራር ለመዘርጋት ስራዎች እየተሰሩ ነው:: ሆኖም የስማርት ስልክ ተጠቃሚዎች መተግበሪያውን በማውረድ በቀላሉ አገልግሎቱን መጠቀም ይችላሉ::

ይህ ፕላትፎርም በዋናነት በአረብ አገራት የሚገኙ ሴቶች ላይ ኢላማ አደርጎ የሚሰራ መሆኑን የምትናገረው ወጣት ዝማሬ፤ በተለይ ሴቶቹ ካለባቸው የስራ ጫናና ህጋዊ ሆነው እስካልተቀመጡ ድረስ ወደ ህክምና ቦታ ሄደው አገልግሎቱን የማግኘት እድላቸው የጠበበ ከመሆኑ አኳያ ከዚሁ ከኢትዮጵያ ትምህርቱንና የምክር አገልግሎቱን ቢያገኙ ተጠቃሚ እንደሚሆኑም ነው የምትናገረው::

ሴቶቹ የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብ አገልግሎቱን በቀላሉ የማግኘት እድል እንደሚኖራቸውም ነው ወጣቷ የምትናገረው:: የአገልግሎት ክፍያውንም ለማሳለጥ እንደቴሌ ብር የመሰሉ የኦንላይን ክፍያ ስርዓት እንደሚዘረጋ ትገልፃለች:: በአረብ አገራት የሚገኙ ሴቶች ደግሞ ለቤተሰቦቻው ገንዘብ እንደሚልኩ ሁሉ ለሚያገኙት አገልግሎት ገንዘብ በመላክ አልያም ደግሞ ‹‹ፔይ ፓል›› በመጠቀም መክፈል እንደሚችሉም ትጠቁማለች::

በተጠቃሚው ዘንድ የዲጂታል እውቀት አለመኖርም አንዱ ችግር መሆኑ ከግምት ውስጥ ገብቶ የዲጂታል ፕላትፎርሙ እንዳለ ሆኖ የቴሌግራም ቦታ በመጠቀም አገልግሎቱን ለብዙሃኑ ተደራሽ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑንም ትጠቁማለች::

የትምህርትና የምክር አገልግሎቱን ጥራት ለማረጋገጥ የህክምና ባለሞያዎቹ በመተግበሪያው ገብተው ከመመዝገባቸው በፊት የሚሞሉት ፎርም እንደሚኖርም ወጣት ዝማሬ ትጠቅሳለች:: እንዲሁም ሃኪሞቹ የሚስማሙበት ህጎችና መመሪያዎች እንደሚኖሩና የህክምና ፍቃዳቸው ጥራት ታይቶ ወደፕላትፎርሙ እንዲቀላቀሉ የሚደረግበት አሰራር ስለመኖሩም ትናገራለች::

በአሁኑ ግዜም የጎግል ፎርም በማዘጋጀት የተወሰኑ ሃኪሞች እንዲመዘገቡ መደረጉንና በቀጣይ ወደስራው ሲገባ ሌሎች ሃኪሞችም በዚሁ ፕላትፎርም ውስጥ እንዲመዘገቡ በማድረግ የሃኪሞቹን ቁጥር የመጨመር እቅድ እንዳለ ትጠቁማለች::

ቴክኖሎጂው በርካታ ስራዎች ሊሰራበት የሚችል ትልቅ ዘርፍ መሆኑን የምትናገረው ወጣት ዝማሬ፤ ልክ እንደእርሷ ሁሉ ሌሎች ወጣቶችም ቴክኖሎጂ ተኮር ስራ ፈጠራዎች ላይ በማተኮር ለህብረተሰቡ መፍትሄ እንዲያመጡ ጠንክረው ሊሰሩ እንደሚገባ ምክሯን ትለግሳለች::

ሚስተር አህመድ ተሃድሪ የቴክ አፍሪካን ዉሜን ፕሮግራም ፕሮጀክት ማናጀር ናቸው:: እርሳቸው እንደሚሉት የስራ ፈጠራ ፕሮግራሙ በአፍሪካ ወጣት ስራ ፈጣሪ ሴቶች አቅም ግንባታ ላይ ያተኮረ ሲሆን ሴቶቹ አዲስ የቢዝነስ ሃሳብ ሲጀምሩ ሃሳባቸው መሬት ላይ እንዲወርድና ገንዘብ እንዲያመነጭ የተለያዩ ድጋፎች ይደረግላቸዋል:: ፕሮግራሙም የተጀመረው እ.ኤ.አ አቆጣጠር በነሃሴ ወር 2022 ነው::

ከዚህ አንፃር በመጀመሪያው ምዕራፍ ከአራት የአፍሪካ አገራት ማለትም ከኢትዮጵያ፣ ታንዛኒያ፣ ሴኔጋልና ቱኒዚያ 331 ወጣት ሴቶች አመልክተው 74ቱን በመምረጥ በካምፕ ሆነው አዲስ ለሚጀምሩት የዲጂታል ቢዝነስ ማጎልበቻ የሶስት ቀን ስልጠና ተሰጥቷቸዋል::

በመቀጠል ደግሞ ከ74ቱ ውስጥ ስምንቱን በመምረጥ ለሶስት ወራት ያህል በኦን ላይን የተለያዩ ትምህርቶችን እንዲከታተሉ በማድረግ የቢዝነስ ሃሳባቸውን እንዲያበለፅጉ ተደርጓል:: ተወዳዳሪዎቹ የተመረጡበት መስፈርት ደግሞ በቢዝነስ ሞዴላቸው ውስጥ ያካተቱት ገበያ መጠን፣ ተወዳዳሪነታቸው፣ ልምዳቸው፣ የጀመሩት ቢዝነስ እንዴት ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል ያቀረቡት ምክንያትና ሊያመጣው የሚችለው በጎ ውጤት ነበር::

በመጨረሻም ስምንቱ ተወዳዳሪዎች የቢዝነስ ሃሳባቸውን በአዲስ አበባ አቅርበው ታንዛኒያዊቷ ጁሊያና ቡሳሲ የተሻለ የዲጂታል ቢዝነስ ሃሳብ በማቅረቧ ተሸላሚ ለመሆን በቅታለች::

በቀጣይ ዓመት በዚሁ ፕሮግራም አማካኝነት ሌሎች ተጨማሪ አስራ ስደስት የአፍሪካ አገራትን ተደራሽ ለማድረግ እቅድ ተይዟል:: ይህም በርካታ የአፍሪካ ወጣት ሴቶች አዳዲስ የዲጂታል ቢዝነስ ፈጠራ ሃሳብ አመንጪዎች በፕሮግራሙ እንዲሳተፉ ይጋብዛል:: በተለይ ደግሞ ወጣት ሴቶች የቢዝነስ ሃሳብ ኖሯቸው ሃሳባቸውን እውን በማድረግ ረገድ ተገቢውን ክህሎት እንዲያገኙ በማስቻል ፕሮግራሙ የጎላ ሚና ይኖረዋል::

ከዚህ ባለፈ ፕሮግራሙ አፍሪካውያን ስራ ፈጣሪዎችን እርስ በእርስ በማገናኘት የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ፣ በገበያ እንዲተሳሰሩና በቅንጅት እንዲሰሩ የላቀ ሚና ይጫወታል::

# የምድር በረከት

## ለውጥ እየታየበት ያለው
## የወርቅ ግብይቱን ከህገወጦች የመታደግ ርብርብ

ስምስም መንግሥቱ



በግብረ ኃይሉ የሚካሄደው የቁጥጥር ስራ ወደ ብሔራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ መጠን እንዲጨምር እያስቻለ ነው

ኢትዮጵያ የምድር ውስጥ ገፀበረከቶቿ በሆኑት የማዕድን ሀብቶቿ ተጠቃሚ ለመሆን ከመቼውም ጊዜ በላይ መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ እያደረገች ትገኛለች። የፖሊሲ ማሻሻያ እርምጃዎች በመውሰድ፣ ለአምራች ኢንደስትሪ፣ ለግንባታና ለጌጣጌጥ የሚውሉ ማዕድኖችን ለይቶና የመገኛ ሥፍራዎችን ጭምር የያዘ ሰነድ ማዘጋጀት፣ የማዕድን ጋለሪ ከፍቶ ለኢንቨስትመንት ምቹት በመፍጠር እየተከናወኑ ያሉ ተግባሮች እየተከናወነ ለሚገኘው ርብርብ በአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት ከዩኒቨርሰቲዎች ጋር ቅንጅት በመፍጠር፣ከባለድርሻ አካላት ጋር ትብብር በመፍጠር በዘርፉ ላይ የሚያጋጥሙ የህገወጥ ግብይትና መሰል ተግዳሮቶችን በጋራ ለመፍታት፣ ዘርፉን ለማዘመን፣ በዘርፉ በተለይም የተፈጥሮ ጋዝና ነዳጅን በውጭ ኩባንያዎች በማስጠናት፣ በማዕድንና ቴክኖሎጂ ኤክስፖ ሀብቱን ለዓለም በማስተዋወቅ የተከናወኑ ተግባሮችም ሌሎች ጥረቶች ናቸው።

የማዕድን ዘርፍ ለበርካታ ዜጎች የስራና የገቢ አማራጭ በመሆን ያገለግላል፤ ስራው በተቀናጀ መልኩ እንዲመራ በማድረግ ለዜጎችም ለሀገርም ይበልጥ እንዲጠቅም ለማደረግ ዘርፉን የሚመራው ማዕድን ሚኒስቴር ከስራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በሰው ሀይል ልማት፣ቴክኖሎጂ፣ ስራ ፈጠራና የስራ አካባቢ ደህንነት ዙሪያ በጋራ ለመስራት ስምምነት ማድረጉ ይታወሳል። እነዚህ ሁሉ ጥረቶች የሚደረጉት የማዕድን ዘርፉ ለሀገር ምጣኔ ሀብት እድገት አስተዋጽኦ እንዲኖረው ለማስቻል ነው።

ይሁን እንጂ የማዕድን ዘርፉ ማነቆ የሆነውን ህገወጥ ንግድ ለመከላከል የተደረገው እንቅስቃሴ ለውጥ ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እየፈጠረ ይገኛል።ለዚህም ወደ ብሄራዊ ባንክ መግባት ያለበት የወርቅ መጠን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየቀነሰ መምጣት አንድ ማሳያ ተደረጎ ሊወሰድ ይችላል።

በአንድ ወቅት የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ ኡማ በባህላዊ የወርቅ ማዕድን ምርት ላይ የተሰማሩትን የአካባቢውን ወጣቶችም ሆኑ ከውጭ ዜጎች ጋር በመመሳጠር የሚደርጉ ህገወጥ እንቅስቃሴዎችን ሥርዓት የማስያዝ ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ መግለጻቸው ይታወሳል።

በቅርቡም ሚኒስቴሩ ካወጣው መረጃ መረዳት እንደተቻለው፤ ሚኒስቴሩ ወደ ቁጥጥር ስራው ገብቷል፤ በጉዳዩ ላይም ማዕድን ሚኒስቴር ማንኛውም ልዩ አነስተኛ የወርቅ አምራች በእጁ ያለውን ወርቅ ወደ ቢሄራዊ ባንክ እንዲያስገባ ያሳሰበ ሲሆን፣ በቀጣይ መንግሥት ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ ወርቅ ወደ ቢሄራዊ ባንክ በማያስገቡት ላይ ህጋዊ እርምጃ እንደሚወሰድ ማስገንዘቡን በድረገጹ አስነብቧል።

ሚኒስቴሩ በፌዴራል ማዕድን ሚኒስቴር የሚመራ የተቀናጀ የማዕድን ቁጥጥር ኦፕሬሽን ቡድንና በጋምቤላ ክልል በዲማ ወረዳ ከሚገኙ ከልዩ አነስተኛ የወርቅ አምራቾች ጋርም ውይይት መደረጉን ታህሳስ 5ቀን2015ዓ.ም በድረገጹ አስነብቧል።

የውይይቱ ዓላማ ህገወጥ የወርቅ ኮንትሮባንድ ንግድን በመቆጣጠር በዲማ ወረዳ የሚመረተው ወርቅ በህጋዊ መንገድ ወደ ብሔራዊ ባንክ እንዲገባ ማስቻል ነው ። የማዕድን ሚኒስቴር በወርቅ ኮንትሮባንድ ዙሪያ እንደ ሃገር አራት ቡድኖችን አደራጅቶ ወርቅ በሚመረትባቸው አካባቢዎች አሰማርቷል፤ ከነዚህ አካባቢዎች አንዱ ዲማ ወረዳ ነው። ከጥቅምት 23 ጀምሮ በስፍራው ተገኝቶ ስራውን የጀመረው ቡድኑ ያሉትን ችግሮች መለየቱንም ሚኒስቴሩ በድረገጹ አመልክቷል።

ከአካባቢው መስከረም ወር ላይ ብሄራዊ ባንክ የገባው የወርቅ መጠን ስድስት ኪሎግራም ብቻ እንደነበርና ቁጥጥሩ ከተጠናከረ በኃላ መጠኑ መጨመሩን መረጃው አስታውቋል። ቡድኑ ባደረገው ቁጥጥር ከአካባቢው በጥቅምት ወር 2015ዓ.ም 10 ኪሎግራም፣ በህዳር ወር 2015ዓ.ም 18 ኪሎግራም ወርቅ ብሄራዊ ባንክ እንዲገባ ማድረግ ተችሏል። ቡድኑ ባደረገው ኦፕሬሽን በኮንትሮባንድ የወርቅ ዝውውር የተጠረጠሩ 11 ግለሰቦች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ተደርጎ ምርመራ እየተደረገባቸው ይገኛል።

በሌላ በኩል በአካባቢው አልፎ አልፎ የሚከሰቱ የፀጥታ ችግሮች፣ህገወጥ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ፣ በመንግሥት በኩል በቂ ቁጥጥር አለማድረግ የሚሉ አስተያየቶችንም የልዩ ልዩ አነስተኛ ወርቅ አምራቾች ማንሳታቸው በዘገባው ተጠቅሷል። በዚህ በኩል መንግሥት የሚጠበቅበትን እንደሚሰራን በሚኒስቴሩ ተገልጿል።

ከወራት በፊት ጀምሮ የወርቅ ልማቱ በሚከናወንበት ዲማ ወረዳ ውስጥ ሆነው ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ካሉት መካከል የጋምቤላ ክልል ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ ዋና የሥራ ሂደት ሃላፊ አቶ ሙድ ሎንግ አንዱ ናቸው። አቶ ሙድ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳሉት፤ ቀደም ሲል እስከ አንድ መቶ ኪሎ ግራም ለብሄራዊ ባንክ ይገባ የነበረው ወርቅ እጅግ ማሽቆልቆሉን አቶ ሙድ ጠቅሰው፣ ይህ የሆነው ወርቅ አምራቾች ያመረቱትን ወርቅ ለጥቁር ገበያ በማቅረብ ከሀገራዊ ጥቅም ይልቅ የራሳቸውን በማስቀደማቸው ነው።

ክፍተቱ የተፈጠረው ከቁጥጥርና ክትትል መላላት መሆኑንም ጠቅሰው፣ ህገወጥነቱ እየከፋ በመምጣቱ በቢሮአቸው ተወክለው ከግብረ ኃይሉ ጋር የመከላከሉን ሥራ ለመሥራት ከጥቅምት ወር መጨረሻ ጀምሮ የወርቅ ልማቱ በሚከናወንበት ዲማ ወረዳ እንደሚገኙ ተናግረዋለ።

ከተለያዩ አካላት ከተውጣጣ ግብረኃይል ጋር በመሆን በፀጥታ ኃይል በመታገዝ ከሶስት ወራት በፊት የተጀመረው የተቀናጀ እና የተጠናከረ የቁጥጥር ሥራ ለውጥ አስገኝቷል ሲሉም ገልጸዋል።

የቁጥጥር ሥራው ከተጀመረ አንስቶ በተከናወነው ተግባር ወደ ብሄራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ መጠን ከ10 ኪሎ ግራም ወደ 18 ኪሎግራም ከፍ ብሏል ሲሉም አቶ ሙድ ተናግረዋል። የቁጥጥር ሥራውን ለመሥራት የተዋቀረው የግብረኃል ቡድን የተጠናከረ ሥራ እንዲሰራ ለተጨማሪ ጊዜ በስፍራው እንዲቆይ መደረጉን ጠቅሰው፣ በዚህም የክትትልና ቁጥጥሩ ስራ መጠናከሩን ይገልጻሉ።

በግብረ ኃይሉ ውስጥ የክልሉ ማዕድንና ሀብት ልማት ቢሮን ጨምሮ ፖሊስ፣ ፍትህ፣ሰላምና ፀጥታ በአጠቃላይ የፀጥታ ኃይል፣ የጉሙሩክ ባለሥልጣን፣ ቱሪዝም ኮሚሽን፣ የወረዳ ተወካዮች ተካትተውበታል ሲሉም ነው ያብራሩት።

በአካባቢው እየለማ ያለው የማዕድን ሀብት ህጋዊ በሆነ አሰራር እንዲመራ ለማስቻል የግብረ ኃይል ቡድን ተዋቅሮ እየተከናወነ ያለው ተግባር በጊዜያዊነት የተወሰደ መፍትሄ መሆኑ ይታወቃል። ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የተቀመጠ አቅጣጫ ይኖር እንደሆን አቶ ሙድ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ እንዳመለከቱት፤ በግብረ ኃይሉ ህገወጥነትን ለመከላከል የተዘረጋው አሰራር በዘላቂነት ለሚወሰደው እርምጃም አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ጠቅሰው፣ ወረዳውና ዘርፉን የሚመራው አካል ተቀናጅተው አሰራሩን ለማስቀጠል ቁጥጥርና ክትትሉ እንዲጠናከር ለማድረግ ጥረት እንደሚደረግ ተናግረዋል። ቢሮውም በየወሩ በሥፍራው በመገኘት ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል ብለዋል።

በአካባቢው ያለው የወርቅ ሀብት እንደ ሀገርም እንደ ክልልም ከፍተኛ የኢኮኖሚ ፋይዳ አለው ያሉት አቶ ሙድ፤ በተለይ እንደ ክልል ለወጣቶች የሥራ እድል ለመፍጠር ትልቅ ተስፋ ተጥሎበታል ነው ያሉት። ሀብቱን በአግባቡ በማልማት በሀገር ደረጃ የተቀመጠውን አሰራር ተከትሎ ግብይቱን መፈጸም እንደሚገባ ክልሉ ያምናል ሲሉም ገልጸዋል። ህጋዊ መስመርን የተከተለ ግብይት የክልሉንም ገቢ በማሳደግ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ጠቅሰው፣ ገቢ በአግባቡ መሰብሰብ ከተቻለ መሠረተ ልማቶችን ለማስፋፋት እንደሚውልም አስረድተዋል።

የጉሙሩክ ኮሚሽንን በመወከል በቡድን በተዋቀረው ግብረኃይል ውስጥ የሚሰሩና ስማቸው እንዲገለጽ ያልፈለጉ አንድ አባል በሰጡት አስተያየት የግብረ ኃይሉ ዋና ተልእኮ የተመረተው የወርቅ ማዕድን ወደ ብሄራዊ ባንክ እንዲገባ ማስቻል መሆኑን ተናግረዋል። ይህን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ መሆኑን ገልጸዋል። በቡድኑ እየተከናወነ ባለው ተግባር ህገወጦችንም ለህግ በማቅረብ ስራውንም ህጋዊ መስመር የማስያዝ ሥራ ጎን ለጎን እየተሰራ ነው ይላሉ።

እርሳቸው እንዳሉት፤ ህገወጥ ሥራ እየተሰራ ስለመሆኑ አመላካች ነገር መኖሩን ቡድኑ ደርሶበታል። በአጭር ጊዜ ውስጥ ችግሩን ሙሉ ለሙሉ መፍታት ተችሏል ማለት ባይቻልም፣ ለውጥ ማምጣት ግን ተችሏል። በህገወጥ ድርጊቱ ተሰማርተው ተገኝተዋል የተባሉ ስድስት ሰዎችንም በቁጥጥር ሥር ማዋል ተችሏል። እነዚህ ግለሰቦች ጥፋተኝነታቸው ከተረጋገጠ ከሁለት አመት እስከ አምስት ወር እንዲሁም ከሶስት አመት እስከ አምስት ወር በእስራት የሚቀጡ ከመሆናቸው በተጨማሪ ከ50ሺ እስከ አንድ መቶ ሺ ብር የቅጣት ውሳኔ ይጠብቃቸዋል።

ከጥቅምት ወር ጀምሮ በግብረኃሉ በተከናወነው ሥራ ወደ ብሄራዊ ባንክ የሚገባው ወርቅ 80 በመቶ መጨመሩንም ነው የግብረ ህይሉ ቡድን አባል የጠቆሙት። ህገወጥነትን ለመከላከል በአንድ ወረዳ ላይ በተጀመረው ሥራ የተገኘው ውጤት ህገወጥነትን ለመከላከል እንደሚቻል አመላካች ሆኖ ተገኝቷል ሲሉም አመላክተዋል። ህገወጥነቱን መከላከል ቢቻል ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ከፍተኛ የሆነ የወርቅ ማዕድን ልማት በአካባቢው መኖሩን ለመታዘብ መቻሉንም ነው የገለጹት።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ህገወጥ ድርጊቱ እዚያው አካባቢ በሚኖሩ አንዳንድ ህገወጦች እንደሚፈጸም በክትትልና ቁጥጥሩ ማረጋገጥ ተችሏል። የአካባቢውን ማህበረሰብ የማስተማርና የማንቃት ሥራ ቢሰራ ችግሩን ለመቀነስ ይጠቅማል። ጉሙሩክ በወጪና ገቢ ንግዶች ላይ የሚያደርገውን የቁጥጥር ሥራ በወርቅ ማዕድን ላይም ማድረግ ይኖርበታል።

በአካባቢው በማህበር ተደራጅተው ወርቅ ለማምረት መሬት ከወሰዱ ወጣቶች ላይ በኪራይ ወስዶ እየሰራ የሚገኘው የአዲቢሩ ድርጅት የሥራ ኃላፊ ወጣት ፖል በግሉ ህጋዊ ሆኖ ኃላፊነቱን ለመወጣት ጥረት እያደረገ መሆኑን ተናግሯል።

ወጣቱ ህገወጥ ድርጊቱን ይቃወማል፤ ድርጊቱ እንዲጠፋም ነው የሚፈልገው። ወርቅ ሀገራዊ ጥቅም እንዲያስገኝ የክትትልና ቁጥጥሩ ሥራ የመንግሥት ብቻ መሆን እንደሌለበት ጠቅሶ፣ አምራቹም፣ የአካባቢው ማህበረሰብም በቁጥጥር ላይ አብረው መሥራት እንዳለባቸው አመልክቷል።

ወጣት ፖል ለህገወጥ ድርጊቱ መስፋፋት ምክንያት ናቸው ያላቸውንም ጠቁሟል። እርሱ እንዳለው፤ ለልማቱ ሥራ የሚያስፈልገው ነዳጅ በአካባቢው ከተመን በላይ እየተሸጠ ነው። በዚህ ዋጋ ነዳጅ እየገዙ መስራት ያስቸግራል። ብሄራዊ ባንክ ከአምራቾች የሚቀበልበት የወርቅ ዋጋም መሻሻል እንዳለበት ጠይቆ፣ አለበለዚያ ምርቱን ጥቁር ገበያው ይቆጣጠረዋል ሲል ስጋቱን ጠቁሟል።

አቶ ሙድ በጋምቤላ ክልል ወርቅ የሚገኝባቸው አካባቢዎች በአኝዋክ ብሄረሰብ ዞን ዲማ፣ አቦቦና ጋምቤላ ወረዳዎች መሆናቸውን ይገልጻሉ። አቦቦ ወረዳ ውስጥ የሚገኘውን የወርቅ ክምችት አካባቢው በደን የተሸፈነና ደኑም በዓለም የባህል የትምህርትና ሳይንስ ድርጅት (ዩኔስኮ) የተመዘገበ በመሆኑ ጥቅም ላይ ማዋል አልተቻለም ሲሉ ያመለክታሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ሌላው ችግር በአካባቢው ውሃ አለመኖሩ ነው። ከመሬት ውስጥ በቁፋሮ የሚወጣውን ወርቅ ከጭቃ ለመለየት ውሃ ያስፈልጋል። መንገድን ጨምሮ የመሠረተ ልማት አለመሟላትም ሌሎች ችግሮች ናቸው። በነዚህ ምክንያቶች ሳቢያ የዚህ አካባቢ ወርቅ ለጊዜው ጥቅም ላይ አልዋለም።

ሌሎች ወረዳዎችም እንዲሁ ተመሳሳይ ችግሮች አሉባቸው። ጋምቤላ ወረዳ ላይ ያለው ችግር ደግሞ በአካባቢው የሚገኘው የባሮ ወንዝ ለከተማዋ የመጠጥ ውሃ ስለሚውል ብክለት በማስከተልና የከተማ ገጽታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያለው ሆኖ በመገኘኑቱ ምክንያት ለማልማት አልተመረጠም።

የወርቅ ማእድን ልማቱ እየተከናወነ ያለው በዲማ ወረዳ ብቻ መሆኑን ጠቅሰው፣ክልሉ በመሳሪያና በተለያየ መንገድ የተደራጀ አቅም ባለመፍጠሩ በዚያ አካባቢ ያለው የወርቅ ሀብት መጠን ለመለየት አልተቻለም ይላሉ። በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ በተደረገ ጥናት ግን በዲማ ወረዳ የተሻለ የደለል ወርቅ ክምችት መገኘቱ ተጠቁሟል ሲሉ ጠቅሰው፣ ይህንንም ክልሉ ጥቅም ላይ እያዋለው ይገኛል ብለዋል።

የወርቅ ልማቱም በስፋት እየተከናወነ ያለው በአካባቢው ማህበረሰብና በማህበር በተደራጁ ወጣቶች በባህላዊና አነስተኛ ወርቅ አምራች በሚባሉት ነው። ስቴላ እና ኢትዮ ኖርዌይ የሚል መጠሪያ ያላቸው ኩባንያዎችም በልማቱ ተሰማርተዋል፤ ስቴላ ወደ ማምረት ገብቷል፤ ይሁንና ግን እሱም በሚጠበቅበት በኩባንያ ደረጃ እያመረተ አይደለም።

ኢትዮኖርዌይም ገና በጥናት ሥራ ላይ ቢሆንም፣ በቅርቡ ሥራ ይጀምራል ተብሎ እየተጠበቀ ነው። በልማቱ ላይ በሚገኙት እየተከናወነ ባለው ሥራ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ጥረት እየተደረገ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የወርቅ ማጠቢያና መቆፈሪያ (ስካቫተር) ዘመናዊ መሳሪያ ወይም ማሽን በመጠቀም የተሻለ እንቅስቃሴ እየታየ ነው።በአካባቢው እየተከናወነ ያለው የወርቅ ማዕድን ልማት የቆየ ቢሆንም፣ ከ2012ዓም ጀምሮ ግን የተሻለ እንቅስቃሴ እየታየ ይገኛል።

ለብሄራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ መጠን እየቀነሰ መምጣቱን ተከትሎ የወርቅ ህገወጥ ግብይትን ለመቆጣጠር በፌዴራል መንግስትና በክልሎች በተቀናጀ መልኩ የተጀመረው ርብርብ ችግሩን መፍታት እንደሚቻል ያመላከት ውጤት እየታየበት ስለመሆኑ የዲማ ወረዳ ተሞክሮ ያመለክታል። ተመሳሳይ ስራዎችን በሌሎች ወርቅ አምራች አካባቢዎች በማከናወን የወርቅ ምርቱን ከህገወጦች መታደግ ያስፈልጋል። ዘላቂ መፍትሄ ማመላከትም ይገባል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የፍቅር ነፍሰ ገዳዮች

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ማታ ሊሆን ትንሽ ሲቀረው..አስራ ሁለት ግድም ላይ ከቤት ወጣሁ ሳሮንን ላገኝ:: ሳሮን ከብዙ የእንገናኝ ውትወታ በኋላ ቃሏን የሰጠችኝ የመጀመሪያዋ ሴት ነች:: ደሞ እኮ አታምርም..ቆንጆ ሆና ብታለፉኝ አይቆጨኝም ነበር:: አስቀያሚ ናት..የሌለ:: በአስቀያሚ ሴት ደጅ ስጸና ሳሮን የመጀመሪያዬ ናት:: አስቀያሚ ከሆነች ምኗን ወደድከው ካላችሁኝ እንዲህ እላችኋለው..ሳሮን የትኛዋም ሴት የሌላት ሁለት ነገሮች አሏት..ኩራትና ንቀት:: እና እጆቿ በጣም ነው የሚያምሩኝ..እግሮቿ እንደ ቤተመቅደስ ሜንጦላይት ጸዐዳ ናቸው:: በተለይ ጉርድ ቀሚስ አድርጋ ስትመጣ (ባትመጣ ነው የሚሻለኝ) የምሆነውን አላውቅም::

አቤት ስትንቀኝ! እንደ ሰው እኮ አትቆጥረኝም:: አጠገቧ ስቆም ወይም ደግሞ ላገኛት ሰፈሯ ስሄድ ወይም ደግሞ ደውዬ ሳወራት የማታደርገኝ የለም:: አንድ ቀን ምን አለችኝ መሰላችሁ ‹በማልመጥንህ በእኔ ጊዜህን ከምታጠፋ ለምን ብጤህን አትፈልግም? አለችኝ:: ምክር ይሆን ራሮት ምን እንደሆነ ዛሬም ድረስ አልደረስኩበትም:: ብቻ ከእሷ ውስጥ ጥሩ ነገር እንደማይወጣ ስለማወቅ ንቀት ነው ስል በሙሉ ደምጽ ተቀብዬዋለው:: አዎ ንቀት ነው..ከንቀት ውጪ ምንም ሊሆን አይችልም:: ስትናገረኝ እንዴት እየሆነች እንደሆነ አስታውሰዋለው:: ራሮት ቢሆን ኖሮ በዛ ቅላጼ፣ በዛ ምጽድቅና፣ በዛ ኩፈሳ፣ በዛ የፊት እንቅስቃሴ አትናገርም ነበር:: ምን እንደነካው እንጨት እንደሚባለው ፊቴን ተጸይፋው..እንድሄድላት በመጋበዝ አይነት ነበር ያናገረችኝ:: ይቺን ሴት ነው ያፈቀርኳት::

እንደፈለገች መሆኛዋ ነኝ..:: ያልተሰደብኩት ስድብ፣ ያልተገላመጥኩት ግልምጫ የለም:: ፍቅሬን ተጠቅማ የቻለችውን ያክል ከፍና ዝቅ አድርጋኛለች:: ራሴን ግልጽ ባደረግ ብዙ የተሰደበ ተብዬ ኒሻን እንደማገኝ አልጠራጠርም:: ግን የፍቅር ስድቦች አያሙም.. አይሰሙም:: ምናልባት ወደፊት ታሪኬን ስገልጽ በነዛ ስድቦች እታመም ይሆናል ለጊዜው ግን መልካም ሁኔታ ላይ ነኝ:: እዚህ ምድር ላይ በሚያፈቅረው ሰው እንደ እኔ የተናቀ እንደ ሳሮንም ሰው የናቀ አለ አልልም:: የንቀትን ጥግ፣ የውርደትን አጽናፍ አይቼዋለው:: ግን በንቀቷ ፊቴ ተቀይሞ፣ ቀልቶና ተሸማቆ አያውቅም:: ብዙ ጊዜ ሰው ባለበት ቦታ ላይ ለዛውም ድምጽዋን ከፍ አድርጋ በሚያዋርድ ክፉ ዋል ተናግራኝ ታውቃለች በነጋታው ግን አጠገቧ ነን..ለሌላ ውርደት:: ይቺን ሴት ነው ያፈቀርኳት::

ራሴ ግራ ተጋብቼ ጓደኞቼንም ግራ አጋብቻለው:: በሳሮን ፍቅር ፈምሻለው..የማያውቀኝ የለም:: እሷም በእኔ በመወደዷ እንደ እኔ ታዋቂ ሆናለች:: ሰፈር ውስጥ የማይጠቋቆምባት የለም.. በእኔ ስም ነው የምትጠራው:: ናሆም ያበደላት ሴት እየተባለች በሄደችበት ሁሉ ይወራላታል:: ከሰፈሯ ራቅ ካለች ደግሞ ‹ያ ቆንጆው ልጅ ያፈቀራት ሴት ናት አይደል?..ታድላ ትባላለች:: እኔ አንድም ቀን እንደ እሷ ታድሎ ተብዬ አላውቅም:: ሰው የሚጠቋቆምብኝ ሞኝነቴን ሊነግሩኝና እንዳው ይሄን የመሰለ ልጅ ምን አስነክታው ነው? ለማለት ነው:: ከፍቅሯ የተረፈኝ ጅላጅልነትና ከንፈር የሚመጠጥለት መሆን ነው:: ይገርመኛል ፍቅር..ይገርመኛል የሰው ልጅ:: ሰው ለመታደል የግድ የምትወደውን መውደድ አለበት? ለመታደል የግድ ቆንጆ ሴት ማፍቀር አለብኝ? ሳሮን እኮ በእኔ ልብ ውስጥ የቆንጆዎች ቆንጆ፣ የውቦች ውብ ናት.. ለምን ታድለህ አይሉኝም? ስል እበሳጫለው:: ፍቅር እውነት ሆኖ ሳለ በራሳችን የፍርድ ሚዛን ባልዋለበት እናውለዋለን:: የእኔን ቁንጅናና የሳሮንን ፉንጋነት ሰማይና ምድር አድርገው ምን ብታስነካው ነው አሉ? በፍቅር ለመውደቅ ምን መነካት ይጠይቃል..?

ሳሮን አፍቅሬ ሳዘባንናት ተፈቅራ አሸማቀቀችኝ:: በዛች ኩራተኛ ነፍስ ፊት ቆሜ ግን አሁንም ፍቅር መልኩ አልጠፋኝም:: ፍቅርን ነውር የምናደርገው እኛ የሰው ልጆች ነን:: ፍቅር ነውር ሆኖ አያውቅም..ዛሬም እንደ ትላንቱ አዲስ ነው..የእየሱስን ስም ይዞ የሚኖር:: መርጠን ስለምናፈቅርና ተመርጠን መፈቀር ስለምንፈልግ ግን ነውር እናደርገዋለን:: ግፍ ነው ብለን መርጠን ከጣልነው እውነት ጀርባ ያለውን ጿጋ ስለማናውቅ እንደ እኔና እንደ ሳሮን አይነት የፍቅር ታሪክ ስንሰማ አፋችንን ለፍርድ እናሞጠሙጣለን::

በአለም ጥግ የአፍቃሪን ያክል ፍቅርን የተረዳ የለም:: ነፍስ ስታፈቅርና ስትፈቀር ሁለት አይነት ናት:: ስናፈቅር ፍቅርን ነን..:: እውነትን ጥበብን፣ ማስተዋልን ድንቁርናንም እየተለማመድን ነው:: ስንፈቀር ግን ደንቆሮ ብቻ ነን:: ብዙ ጊዜ የማይገባን አንዳንድ ጊዜ የሚገባን:: ስናፈቅር እንደ እየሱስ ባለማዕረግ ነን...በህይወታችን መቼም እንዴትም የማይጎበኘን የሆነ አዲስነት እየተዋሃደን ነው:: ስንፈቀር ከጽድቅ ይልቅ ለስህተት የተጋለጥን ነን...እየሄድን የማንደርስበት ብዙ ነገር አለን:: እኔና ሳሮን፣ እኔና ታዛቢው፣ እኔና አሽሟጣጩ ፣ እኔና ወጪ ወራጁ፣ እኔና መንገደኛው፣ እኔና ሳሮንን ለምን አፈቀርካት የሚሉኝ፣ እኔና በሳሮን ፍቅር እንደ እብድ የሚያዩኝ፣ እኔና ሳሮን ምን አስነክታው ነው የሚሉ፣ እኔና የሚስቁብኝ፣ እኔና በማፍቀሬ የሚዘባበቱ፣ እኔና በሳሮን ፍቅር ሞኝ የሚሉኝ፣ እኔና የሚቀልዱብኝ ሁለት አይነት ነን..የገባንና ያልገባን::

አለም ሁሉ በአንድ ድምጽ በማፍቀሬ ቢስቅብኝ ሳሮንን ከመከተል አልቆምም:: ለፍቅር የማይሆን ብዙ ነገር እያላት ነው የምከተላት:: የትም ቦታ አይቼው ያልማረከኝ ኩራትና ማንአለብኝነት አላት:: በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ወደ እሷ እሄዳለው:: ከሰባት ወር ስድብና ንቀት በኋላ ዛሬ ልታገኘኝ ፍቃዷን ሰጥታኛለች::

አትኖርም እያልኩ እየሰጋሁ ካለችኝ ቦታ ደረስኩ:: ለሁልጊዜ በሚገርመኝ ሁኔታ ባለችኝ ሰዐት ላይ እየጠበቀችኝ አገኘኋት:: እንዴት ደስ እንዳለኝ አትጠይቁኝ...ጉንጭዋን ስመኘው እጄን ሰላም አለችኝ:: ጣቶቿ ነኩኝ..:: በህልሜ በሚመጡ እጆቿ ተጨበጥኩ:: በቆምኩበት አንድ ጸሎት ጸለይኩኝ በእንዛ እጆች ለዘላለም ለመዳበስ፣ ለዘላለም ለመነካት፣ ለዘላለም ለመጨበጥ:: እጆቿ ይለሰልሳሉ..እንደ መልኳ አይጎረብጡም::

ወንበር ስቤ አጠገቧ ልቀመጥ አይኔን ስቀይስ ሁለት ወንዶች ስሟን እያቆላመጡ ከበስተኋላዬ ሲመጡ ሰማሁ:: ገና እኮ አልተቀመጥኩም፣ ገና እኮ መቀመጫየ ወንበር አልነካም..ገና እኮ በመምጣቷ ተደስቼ አላበቃሁም..በሁለት ወንዶች ተጨበጠች:: ተጨብጣ ብታበቃ ጥሩ ነበር ሰባት አመት ስመኘው ያላገኘሁትን ጉንጩዋን ሳሙት..አንገቷን ተጠመጠሙበት::

‹አቤት የሰው ፍቅር› አልኩ በሆዴ::

የሚሄደው የሚመጣው እጅ ይነሳታል፣ ይስቅላታል.. ይጠመጠምባታል:: ማንም እየተነሳ በሚጨብጠው እጇ ቀናሁ:: አጠገቧ ሆኜ ሰባት ወንድ ጉንጩዋን ስመው..

‹ስንቱን ነው የምታውቀው? ሆቴላቸው ነው እንዴ የቀጠረችኝ? ስል አሰብኩ::

የረሳችኝ መሰለኝ..‹በቃ አፍቃሪ መቀለጃ ሆኖ ቀረ? አልኩ ደግሜ::

ወደ እኔ ዞረች..

‹እና ይሄውልህ..እእእ..

‹ይቅርታ ማነበረ ስምህ?

ስሜ ጠፋባት..ሰባት ወር የተከተላትን ወንድ ስም:: ነፍሴ ተቀየመቻት..ከሰባት ወር በኋላ ላመል ቅያሜ ወደ ውስጤ ሰረገ..

‹ናሆም..› ስል መለስኩላት

‹ይሄውልህ ናሆም..እዚህ የጠራውህ ..› አለች ሆቴሉ ውስጥ ወዳሉት ወንዶች እየጠቆመች ‹በነዚህ ሁሉ ወንዶች የተከበብኩ እንደሆንኩ እንድታውቅ ነው:: በአንተ መፈቀሬን ሳስብ ራሱ ይደብረኛል..እንድታፈቅረኝ አልፈልግም› ብላኝ ትታኝ ወጣች::

ልጋብዛት..ብዙ ብር ተበድሬ ነበር..

# ዓለም አቀፍ



የዩክሬን ፕሬዝዳንት ዘለንስኪና የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ባይደን

## አሜሪካ ለዩክሬን የአንድ ነጥብ 8 ቢሊዮን ዶላር ጦር መሳሪያ ልትሰጥ ነው

አሜሪካ ለዩክሬን ተጨማሪ የአንድ ነጥብ 8 ቢሊዮን ዶላር ጦር መሳሪያ እንደምትሰጥ ገለጸች።የፕሬዝዳንት ዘለንስኪን ጉብኝትን ተከትሎ አሜሪካ ከዚህ ተጨማሪ የጦር መሳሪያ ድጋፍ እንደምታደርግ አስታውቃለች፡፡የሩሲያ ዩክሬን ጦርነት ከተጀመረ 10 ወራት የሞላው ሲሆን ጦርነቱ በየጊዜው በአዳዲስ መልኮችን ማሳየቱን ቀጥሏል።

በአሜሪካ እና አውሮፓ ህብረት የሚመራው ጥምረት ዩክሬን የሩሲያን ጦር እንድትመክት የጦር መሳሪያ፣ ጥሬ ገንዘብ እና ወታደራዊ መረጃዎችን መስጠታቸውን ቀጥለዋል።አሜሪካ ብቻዋን ጦርነቱ ከተጀመረበት ካሳለፍነው የካቲት ወር ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት ለዩክሬን 22 ቢሊዮን ዶላር ገደማ ዋጋ ያላቸው የጦር መሳሪያዎችን ለግሳለች።

አሁን ደግሞ አንድ ነጥብ 8 ቢሊዮን ዶላር ዋጋ ያላቸው ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎችን ለዩክሬን ለመስጠት መወሰኗን ሮይተርስ ዘግቧል።የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚንስትር አንቶኒ ብሊንከን ድጋፉን አስመልክተው እንዳሉት "ሩሲያ የቅዝቃዜ ወራትን እንደ አጋጣሚ በመጠቀም ዩክሬናዊያንን በብርድ ለመቅጣት እየሰራች ነው" ብለዋል።

ዩክሬን ከሩሲያ የሚቃጡባትን የአየር ላይ ጥቃቶች እንድትቋቋም አሜሪካ እና አጋሮቿ የጦር መሳሪያ እና ሌሎች ድጋፎችን ይቀጥላሉ ሲሉም ብሊንከን አክለዋል።የዩክሬን ፕሬዝዳንት ቮሎዶሚር ዘለንስኪ በትናንትናው እለት በሚስጢር ወደ ዋሽንግተን ያቀኑ ሲሆን ከፕሬዝዳንት ጆ ባይደን ጋር በመወያየት ላይ ናቸው።የፕሬዝዳንቱን ጉብኝት ተከትሎም አሜሪካ አዲስ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ ድጋፍ እንደምታደርግ በዘገባው ላይ ተጠቅሷል።

ሩሲያ በበኩሏ ለዩክሬን የሚደረግ የጦር መሳሪያ ድጋፍ እንዲቆም አሳስባ ድጋፉ በዚሁ ከቀጠለ ከአሜሪካ ጋር የቀጥታ ጦርነት ሊጀመር እንደሚችል አስጠንቅቃለች።አሜሪካ ለዩክሬን እሰጣለሁ ካለቻቸው የጦር መሳሪያዎች መካከል የአጭር ርቀት ተምዘግዛጊ ሚሳኤል ጥቃቶችን መፈጸም እና ማምከን የሚያስችሉ ባልስቲክ ሚሳኤሎችን ያካትታል ተብሏል።

የኔቶ አባል ሀገራት ለዩክሬን የጦር መሳሪያ ሲሰጡ ቢቆዩም አብዛኞቹ ሀገራት አሁን ላይ ልገሳቸውን ያቆሙ ሲሆን የጦር መሳሪያ ክምችታቸው መመናመኑ ደግሞ ድጋፉን ለማቆማቸው ዋነኛው ምክንያት መሆኑን አል ዐይን ዘግቧል።

## ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን በዩክሬኑ ጦርነት አገራቸው ተጠያቂ አይደለችም አሉ



የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን በዩክሬኑ ጦርነት አገራቸው ተጠያቂ እንዳልሆነች ተናገሩ።ሁለቱም ሃገራት “አሳዛኝ ሁኔታን እየተጋሩም” ነው ብለዋል፡፡ ፕሬዚዳንቱየሩሲያው ፕሬዝዳንት ከከፍተኛ ወታደራዊ ባለስልጣናት ጋር በመሆን በአገሪቱ ቴሌቭዥን ጣቢያ ባደረጉት ንግግር ዩክሬንን እንደ "ወንድማዊ ሃገር" መመልከት እንደሚቀጥሉም ነው የገለጹት።

ጦርነቱ "የሶስተኛ ሀገራት ፖሊሲ ውጤት" እንጂ የሩሲያ ፖሊሲ አይደለም ሲሉም አቋማቸውን አስረድተዋል።ከዚህ ቀደምም ለጦርነቱ መነሳት መንስኤው የምዕራባውን መስፋፋት እንደሆነ ከሩሲያ በኩል በተደጋጋሚ ሲጠቀስ ይሰማል።ፕሬዚዳንት ፑቲን ዩክሬንን ጨምሮ የሶቪየት ህብረት አባል የነበሩ ሃገራት ምዕራባውያን ሃገራት በፕሮፓጋንዳቸው ቀይረዋቸዋል ብለዋል።

“ለዓመታት ብድርና ርካሽ ኃይል በመለገስ ከዩክሬን ጋር ጥሩ ጉርብትና ለመፍጠር ሞከርን፤ ግን አልሰራም” ሲሉም አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።“እኛ የምንወቀስበትም ሆነ የምንከሰስበት ምንም ነገር የለም።ሁልጊዜም ዩክሬናውያንን እንደ ወንድም ህዝቦች ነው የምናያቸው እና አሁንም እንደዛ ይመስለኛል ፤"አሁን እየሆነ ያለው አሳዛኝ ነገር ነው። ነገር ግን የእኛ ጥፋት አይደለም." ሲሉም አጽንኦት ሰጥተዋል።

ፕሬዚዳንቱ ንግግራቸውን በሚያደርጉበት ወቅትም ወታደራዊ ባለስልጣናቱ በመጪው የአውሮፓውያኑ አዲስ ዓመት ሃገራቸው የጀመረችውን “ልዩ ወታደራዊ ዘመቻ” እንደምትቀጥልም ቃል ገብተዋል።ፕሬዝዳንት ፑቲን አክለውም ሩሲያ ለዚህ ዘመቻ የምታወጣው የገንዘብ መጠን ገደብ እንደሌለው ተናግረዋል።

የመከላከያ ሚኒስትሩ ሰርጌይ ሾይጉ በበኩላቸው አስገዳጅ የሆነውን የሩሲያ ወታደራዊ አገልግሎት የዕድሜ ገደብ ለማስፋትም ሐሳብ አቅርበዋል።በአሁኑ ወቅት ባለው የሩሲያ ህግ መሰረት ከ18-27 ዕድሜያቸው የሆኑ ሩሲያውያን ለግዳጅ የውትድርና አገልግሎት ሊጠሩ ይችላሉ ። ሆኖም የመከላከያ ሚኒስትሩ ያቀረቡት ዕቅድ ከ21-30 ዕድሜያቸው የሆኑ ዜጎችን እንዲያጠቃልል ነው።

ሩሲያ በተቆጣጠረቻቸው ሁለት የዩክሬን ወደብ ከተሞች በርዲያንስክ እና ማሪዮፖል ላይ የጦር ሰፈር ለሚቋቋም መታቀዱን ሚኒስትሩ መግለጻቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።በአሁኑ ጊዜ የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቮልድሚር ዘለንስኪ ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላ የመጀመሪያውን የዋሽንግተን ጉብኝት እያደረጉ ባለበትም ጊዜ ነው መግለጫው የሰጡት።

ዜና

# የሥነ ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን የሀብት ምዝገባ መረጃን እስካሁን ለሕዝብ ክፍት አላደረገም

- የሕዝብ ዕምባ ጠባቂ ተቋም

# የዕንባ ጠባቂ ትችት አዋጁን ካለመረዳት የመነጨ ነው

- የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

**ሃይማኖት ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሀብት ምዝገባ መረጃን ለመረጃ ጠያቂ እንሰጣለን ከማለት ውጪ እስካሁን የምዝገባ መረጃን ለሕዝብ ክፍት አለማድረጉን የዕምባ ጠባቂ ተቋም አስታወቀ። የሥነ ምግባር እና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን በበኩሉ የዕንባ ጠባቂ ትችት ከአዋጁ ጋር የማይሄድና አዋጁን በአግባቡ ካለመረዳት የመነጨ ነው ብሏል።

በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የመረጃ ነፃነት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ማናዬ አለሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሀብት ምዝገባ መረጃን ለመረጃ ጠያቂ እንሰጣለን ከማለት ውጪ እስካሁን የምዝገባ መረጃን ለሕዝብ ክፍት አላደረገም።

አቶ ማናዬ እንዳሉት፤ የሀብት ምዝገባው በአዋጅ ቁጥር 668/2002 ዓ.ም ላይ በተቀመጠው መሠረት እየተፈጸመ አይደለም። የፌዴራል የሥነ ምግባር ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በአዋጁ ላይ በተቀመጠው ድንጋጌ መሠረት የተሿሚ፣የተመራጭ እና የመንግሥት ሠራተኞችን ሀብት የመመዝገብና የማሳወቅ ስልጣን አለው። የተመዘገበውን መረጃ ለመረጃ ጠያቂ እንሰጣለን ከማለት ውጪ እስካሁን የምዝገባ መረጃን ለሕዝብ ክፍት አላደረገም።

ተቋሙ ሰሞኑን ባወጣው ሪፖርቱ ላይ እንዳመለከተውም የሀብት ማስመዝገብና ማሳወቅ ሥርዓቱ እየተከናወነ የሚገኘው በኮሚሽኑ በተፈጠሩ ሚስጥራዊ ኮምፒተር ኮድ በመሆኑ በየተቋማቱ የሚገኙ የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች የሀብት ምዝገባ መረጃን ሲጠየቁ ማን ምን እንዳስመዘገበ እንደማያውቁና ምስጢር በመሆኑ መረጃ መስጠት ተቸግረዋል።

በሕጉ አግባብ ኮሚሽኑም የተመዘገቡ ሀብት መረጃዎችን አደራጅቶ በአንድ ቦታ በማስቀመጥ በየተቋማት ውስጥ ያሉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች መረጃ ለጠየቀው አካል መረጃ የመስጠት ግዴታ አለባቸው ሲሉም ነው አቶ ማናዬ ያስታወቁት።

በፌዴራል የሥነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን የሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ተስፋዬ ሻኔቦ በበኩላቸው፤ የዕንባ ጠባቂ ትችት ከአዋጁ ጋር የማይሄድና አዋጁን በአግባቡ ካለመረዳት የመነጨ ነው ብለዋል።

በፌዴራል የሥነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን የሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ተስፋዬ ሻኔቦ በዚህ ጉዳይ ለኢፕድ በሰጡት ማብራሪያ፤ ተቋሙ ያወጣው ሪፖርትም ሆነ የቀረበው ትችት አዋጅ ቁጥር 668/2002ን በሚገባ ያላገናዘበና ኮሚሽኑም የማያውቀው እንደሆነ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ተስፋዬ ማብራሪያ፤ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 12 ላይ እንደተቀመጠው የተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የሀብት ምዝገባ መረጃን ለሕዝብ ክፍት ማድረግና በየሁለት ዓመቱ ስለተከናወነው የሀብት ምዝገባ አጠቃላይ መረጃ በሪፖርት መልክ ይወጣል። እንዲሁም የምዝገባ መረጃን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በጽሑፍ ጥያቄ ሲያቀርብ ኮሚሽኑ መረጃውን የመስጠት ግዴታ አለበት። እስካሁን የሀብት ምዝገባውን የተመለከተ መረጃ የጠየቀ ባለመኖሩ መስጠት አልተቻለም።

በየተቋማት ያሉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችም በአዋጁ መሠረት መረጃ የመስጠት ስልጣን የላቸውም ያሉት ኃላፊው፤ መረጃ መስጠት የሚችለው ኮሚሽኑ ብቻ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች ሥራቸው ሰዎች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ግንዛቤ መፍጠርና ወቅታዊ ሁኔታዎችን ተከታትለው ለኮሚሽኑ ማቅረብ ነውም ብለዋል አቶ ተስፋዬ።

የተመዘገበን ሀብት በተመለከተ ማንኛውም ሰው በጽሑፍ ጥያቄ ሲያቀርብ ኮሚሽኑ መረጃውን ይሰጣል ሲሉም አቶ ተስፋዬ አብራርተዋል።

ኮሚሽኑ እስካሁንም በፍትሕ አካላት፣በፖሊስ እንዲሁም በገቢዎች በሙስና ወንጀል ተጠርጣሪ የሆኑ አካላትን መረጃ ሲጠየቅ ሲሰጥ ቆይቷል ፤ ይሁን እንጂ እስካሁን በግል በመምጣት የተመራጭ ወይም የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችን የሀብት ምዝገባ መረጃን የጠየቀ አካል የለም ሲሉም ተናግረዋል።

እንደ ኃላፊው ገለፃ እስካሁን በፌዴራል ደረጃ ወደ 900 ሺህ ሰዎች በሰነድ ሀብታቸውን ያስመዘገቡ ሲሆን ከ2014 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ ግን ምዝገባውን በዲጂታል መንገድ በማካሄድ ላይ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ የበላይ አመራሮችና ኃላፊዎች በየተቋሙ ምዝገባውን በማድረግ ላይ ይገኛሉ ብለዋል።

እነዚህ ሀብታቸውን ያስመዘገቡ ሰዎችም በየሁለት ዓመቱ ምዝገባውን እንደሚያሳድሱና መሥሪያ ቤታቸውን ሲለቁም እንደሚያሳድሱ ኃላፊው ጨምረው ገልፀዋል።

## የሰላም ስምምነቱ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

እንደ አገር በሁሉም መስክ ተወዳዳሪ ለመሆን ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች ለመተካት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ መንግሥት የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው እንዲያመርቱ ለማድረግ የተለያዩ ማበረታቻዎችን አቅርቧል።

በትናንትናው ዕለት ስምምነት ፈርመው ወደ ሥራ የሚገቡት ሀገር በቀል አምራች ኩባንያዎችም ለዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማድረግ፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለመተካትና ምርታቸውን ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት ትልቅ ሚና እንደሚኖራቸው ገልጸዋል።

ኮርፖሬሽኑ በቀጣይነትም የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶችን በመደገፍ ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው እንዲያለሙና ለዜጎችም የሥራ እድል እንዲፈጥሩ የሚያደርገውን ሥራ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቅሰው፤ መገናኛ ብዙኃንም እንደ ሀገር ያሉትን የኢንቨስትመንት አማራጮችና ምቹ ሁኔታዎች በማስተዋወቅ በኩል ሚናቸውን እንዲወጡ ጠይቀዋል።

ኩባንያዎቹን በመወከል የስምምነት ፊርማውን የፈጸሙት የየኩባንያዎቹ የሥራ ኃላፊዎችም በገቡት ውል መሠረት በቶሎ ወደ ሥራ ለመግባትና ለዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ያላቸውን ዝግጁነት ገልጸዋል።

በድምር ከ11 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል አስመዝግበው ሼድና የለማ መሬት ተከራይተው በኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው መሥራት የሚያስችላቸውን የውል ስምምነት የተፈራረሙት አገር በቀል ኩባንያዎች ጉምሳ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ ሱጂ ሊያና ዶዮ ማኑፋክቸሪንግና ኢምፓክት ፕሪንቲንግና ግራፊክስ ሲሆኑ፣ በሙሉ አቅማቸው ወደ ሥራ ሲገቡ ከ600 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል እንደሚፈጥሩ ተገልጿል።

# ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃን ለማጥራት

በርካታ ውጣ ውረዶች ከሚገጥማቸው ዘርፎች መካከል የትምህርቱ ዘርፍ አንዱ ነው።ለበርካታ ዓመታት የተደራረቡ ችግሮች መኖር የትምህርት ጥራት ላይ ተጽዕኖ ከመፍጠር ባሻገር በነገው ሀገር ተረካቢ ትውልድ ላይ የሚያሳርፈው ጠባሳ ቀላል የሚባል እንዳልሆነ ይታወቃል።ለችግሩ የመንግሥትም ይሁኑ የግል የትምህርት ተቋማት ድርሻቸው ከፍተኛ እንደሆነም የሚገለጽ ሲሆን፤ ከሚስተዋሉት ችግሮች አንዱ ደግሞ ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ መበራከት ነው። የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት ግለሰቦችና አስመራቂ የትምህርት ተቋማት ላይ ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ እየተሠራ መሆኑን የትምህርት እና ሥልጠና ባለሥልጣን ከዚህ ቀደም መግለጹ ይታወሳል። ባለስልጣኑ የትምህርት ጥራትን ከመቆጣጠር ባሻገር የትምህርት ማስረጃ ትክክለኛነትን የማረጋገጥ ሥራን የሚያከናውን ሲሆን፤ በዚህም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማቱ የተማሪዎቻቸውን ዝርዝር መረጃና የትምህርት ማስረጃ ከምዝገባ እስከ ምረቃ ድረስ ለባለሥልጣኑ የመላክ ግዴታ እንዳለባቸውም ካሳወቀም ሰነባብቷል።

በአሁን ወቅት ደግሞ በፌዴራልና በክልል የመንግሥት ተቋማት በሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ተቀጥረው የሚሠሩ ግለሰቦችን ለማጥራት በትብብር እየተሠራ መሆኑን ባለሥልጣኑ አስታውቋል። የባለሥልጣኑ የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሪት ማርታ አድማስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ተቋሙ ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃን ለማጥራት በሚሠራው መጠነ ሰፊ ሥራ ከፌዴራልና ከክልል ተቋማት ጋር በቅንጅት እየሠራ ይገኛል።

እንደ ማርታ ገለጻ፤ የፌዴራልና የክልል ተቋማት አዲስ የሰው ኃይል ቅጥር ሲፈፅሙ እና የደረጃ ዕድገት ሲሠጡ የሠራተኞችን የትምህርት ማስረጃ ሐሰተኛ መሆንና አለመሆኑ እንዲጣራላቸው ወደ ተቋሙ መላካቸው አብረው የመሥራት ቁርጠኝነታቸውን ያሳያል። እንደማሳያም የደበብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ከክልል እስከ ወረዳ ያለው የመንግሥት መዋቅር ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃን በማጋለጥና በማጥራት ሂደት ቀዳሚ እንደሆነ በመጠቆም፤ በተጨማሪም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል፣ የጤና ሚኒስቴር፣ የጉምሩክ ኮሚሽን፣ ማዕከላዊ ስታስቲክስ እና ሌሎች የፌዴራልና የክልል ተቋማት ከትምህርት እና ሥልጠና ባለሥልጣን ጋር በቅርበት እየሠሩ መሆኑንም ያስረዳሉ።

> **በተጨማሪም የግል የትምህርት ተቋማት በአንድ የሙያ ዘርፍ ከተፈቀደላቸው የተማሪ ቁጥር በላይ አልፈው ሲያሰለጥኑ ከተገኙ ተማሪዎች ብቻ መቀጣታቸው ቀርቶ ተቋማትንም ለመቅጣት ከፍትሕ አካላትና ከፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ጋር ለመሥራት መታቀዱን ያነሳሉ**



ወይዘሪት ማርታ አድማስ

ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃን ለማጥራት ተማሪዎች ሀገር አቀፍ ፈተና ወስደው የፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር ያስቀመጠውን ከፍተኛ የግል ትምህርት ተቋም መግቢያ ነጥብ ማምጣታቸውንና መረጃ ተቀብሎ የማጥራት ሥራ እየሠራ መሆኑን ያብራሩት የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሪት ማርታ፤ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ወስደው ለከፍተኛ የመንግሥት ትምህርት ተቋም መግቢያ ነጥብ ያላመጡ ተማሪዎች በግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ገብተው እንዲሠለጥኑ ትምህርት ሚኒስቴር ያወጣው የግል ተቋማት መግቢያ ነጥብ መኖሩንም ያስረዳሉ።ተማሪዎች የግል የትምህርት ተቋማትን ሲቀላቀሉ የትምህርት ሚኒስቴር ያወጣውን ነጥብ አሟልተው መግባታቸውን ለማጥራት የተማሪዎችን ሰነድ እየፈተሹ እንደሆነ የገለጹ ሲሆን፤ አያይዘውም መስፈርቱን ሳያሟሉ በተገኙ ተማሪዎች እና ከተፈቀደላቸው የማስተማር፣ የፕሮግራም እንዲሁም የቁጥር ፍቃድ ውጭ እየተቀበሉ በሚያሠለጥኑ የግል ተቋማት ላይ ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ መረጃ በማሰባሰብ ላይ መሆኑን ይገልጻሉ።

በተጨማሪም የግል የትምህርት ተቋማት በአንድ የሙያ ዘርፍ ከተፈቀደላቸው የተማሪ ቁጥር በላይ አልፈው ሲያሰለጥኑ ከተገኙ ተማሪዎች ብቻ መቀጣታቸው ቀርቶ ተቋማትንም ለመቅጣት ከፍትሕ አካላትና ከፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ጋር ለመሥራት መታቀዱን ያነሳሉ። እንዲሁም ባለስልጣኑ የማስተማር ፍቃድ እና የሚሰጣቸው የፕሮግራም ፍቃድ የማጣራት ሥራ እየተሠራ ሲሆን፤ ሕብረተሰቡም ስለጉዳዩ ግንዛቤ እንዲኖረው ማንኛውንም የሚዲያ አውታር በመጠቀም ግንዛቤ እንዳስጨበጠና በማስጨበጥ ላይ እንደሆነ ወይዘሪት ማርታ ያብራራሉ።

ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃን ለማጥራት የፌዴራል መንግሥት በተለያየ ዘርፍ ከባለሥልጣኑ ጋር እየሠራ መሆኑን እና ወደፊትም በቁርጠኝነት ለመሥራት ጥናት እየተደረገ እንደሆን የጠቆሙት ወይዘሪት ማርታ፤ ትውልድ ገዳይ የሆነውን ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ለማጥራት መንግሥት፣ ሕብረተሰቡ እና መገናኛ ብዙኃን ችግሮችን በማጋለጥ የበኩላቸውን እንዲወጡ መልክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ስፖርት





# እጅ ያጠረው የእጅ ኳስ ፌዴሬሽን

አስማየሁ ግዛው

በርካታ የስፖርት አይነቶች በኢትዮጵያ ጥሩ እንቅስቃሴና እድገት እንደነበራቸው በሚነገርበት 1970ዎቹ የእጅ ኳስ ስፖርት ትልቅ ስም ነበረው። የኢትዮጵያ እጅ ኳስ ስፖርት ፌዴሬሽንም የተቋቋመው በ1970 ሲሆን ወርቃማ ዘመኑም በነዚህ ዓመታት እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህ ሌሎች አገራት ኦሊምፒክን በመሳሰሉ ታላላቅ መድረኮች ከተሳትፎ በዘለለ ወርቅ የሚመዘገብበት ስፖርት አሁን ላይ በኢትዮጵያ እንቅስቃሴና እድገቱ እዚህ ግባ የማይባል ቢሆንም በአንድ ወቅት ኢትዮጵያን በአፍሪካና በአለም ታላላቅ መድረኮች ስሟን ማስጠራት የቻለ ነው።

ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ በተመሰረተበት ጊዜ ስፖርቱ በአዲስ አበባ ብቻ ይካሄድ እንደነበር ይነገራል:: ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ በ1971 የአለም ዓቀፉ እጅ ኳስ ፌዴሬሽን አባል መሆኗን ተከትሎ በ1972 በጀርመኗ ሙኒክ ከተማ በተዘጋጃው ኦሊምፒክ ሳይቀር ኢትዮጵያ መሳተፏን የሚጠቁሙ መረጃዎችም አሉ። የደርግ መንግስት ወደስልጣን ከመምጣቱ ጋር ተያይዞም በሚሊተሪ ተቋማት ውስጥ በርካታ ስፖርቶች ለሁለት አስርት ዓመታት የተሻለ እንቅስቃሴ ሲደረግባቸው እጅ ኳስ አንዱ ነበር። ለዚህም ስፖርቱ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ክለቦችን በማወዳደር ጥሩ የእድገት ጎዳና ላይ እንደነበር ማሳያ ተደርጎ ይጠቀሳል።

የኢትዮጵያ እጅ ኳስ ስፖርት እንደ አብዛኞቹ ስፖርቶች ሁሉ ባለፉት ሰላሳ አመታት ሽቅብ እንደ ማሽላ ከማደግ ይልቅ ቁልቁል እንደ ካሮት ማደጉ የአደባባይ ሃቅ ነው። ፌዴሬሽኑን በተለያዩ ጊዜያት የመሩ ሰዎች ስፖርቱን ለማሳደግ የተለያዩ ጥረቶችን እንደሚያደርጉ ቢናገሩም መሬት ላይ ጠብ ያለ ነገር የለም። በየትኛውም ጊዜ ፌዴሬሽኑን የመሩ ሰዎች የሚጋሩት አንድ ነገር ግን ተደጋግሞ ይነሳል። ይህም እጅ ኳስን ለማሳደግ እጅ አጥሮናል የሚል ነው።



**ፌዴሬሽኑ በቂ በጀት ባይኖረውም ስፖርቱን ለማሳደግ ባለፉት 7 ዓመታት የፕሪሚየርሊግ ውድድሮች እያካሄደ ነው፣**

የኢትዮጵያ እጅ ኳስ ፌዴሬሽን ባለፉት በርካታ አመታት ከበጀት እጥረት ጋር በተያያዘ ማደግ ባለበት ደረጃ ባይጓዝም አንድ አበረታች ጅምር ካለፉት ሰባት አመታት ወዲህ ማሳየቱ አይካድም። ይህም በዘወትር ችግሩ የበጀት እጥረት እየተፈተነም ቢሆን በአገር አቀፍ ደረጃ ክለቦችን በፕሪሚየርሊግ ማወዳደሩ ሲሆን ዘንድሮም ይህንኑ ውድድር ለሰባተኛ ጊዜ እያከናወነ ይገኛል።

የኢትዮጵያ እጅ ኳስ ፌዴሬሽን ጽህፈት ቤት ኃለፊ አቶ ሞላ ተፈራ፣ የእጅ ኳስ ስፖርትን ለማሳደግ እና ከኢትዮጵያ አልፎ በምስራቅ አፍሪካ እንዲሁም በመላ አፍሪካና በአለም አቀፍ መድረኮች ተፎካካሪ ለማድረግና ብቁ ስፖርተኞችን ለማፈራት ጥረት እያደረገ መሆኑን ለአዲስ ዘመን ገልጸዋል:: ለዚህም የፌዴሬሽኑ የዘወትር እንቅፋት ከሆነው የበጀት እጥረት ለመላቀቅ የተለያዩ ሙከራዎችን እያደረገ ይገኛል። "ከመንግስት የሚመደበው በጀት በቂ ባለመሆኑ ከሌሎች ስፖንሰር አድራጊዎች ጋር በመስራት ስፖርቱን ለማገዝ ጥረት እየተደረገ ነው" ያሉት የጽህፈት ቤት ሃላፊው፣ በቂ ባይሆንም ከባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በተጨማሪ የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ድገፍ እንደሚያደረግለቸው ገልጸዋል። ሌሎችም የነዚህን ተቋማት አርአያ በመከተል ድገፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል። ከዚሁ ጋር አያይዘው የጽህፈት ቤት ሃላፊው እንደተናገሩት "ስፖንሰር ለማግኘት ብዙ አስቸጋሪ ጉዳዮች አሉ፣ ተቋማትና ድርጅቶች ስፖርቱን በገንዘብ ለመደገፍ ሳይንሳዊና ምክንያታዊ ከማቅረብ ይልቅ ከጥቅም ጋር የማገናኘት ነገር ይታያል" ::

ለስፖርቱን ለማንቀሳቀስና ውድድሮችን በስፋት ለማካሄድ ትልቅ የበጀት እጥረት እንዳለ የጠቆሙት አቶ ሞላ፣ አሁን ክለቦች የሚወዳደሩበትን ፕሪሚየርሊግ እንኳን ከመንግስት ውስን በጀትና ከተወሰኑ ስፖንሰሮች ከሚገኘው ገቢ በተጨማሪ በውድድሩ የሚሳተፉ ክለቦች እያንዳንዳቸው 60ሺ ብር ከፍያ ፈጽመው እንደሚወዳደሩ ተናግረዋል:: ይህም ከክለቦች የሚገኘው ክፍያ ለውድድሩ ማካሄጃ እንደሚውል አስረድተዋል። ይህን ችግር ተረድተውም የሚመለከታቸው አካላት ስፖርቱን እንዲደግፉ አቶ ሞላ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል::

ከፕሪሚየርሊጉ ውድድር በተጨማሪ ስፖርቱን መሰረት ለማስያዝና እድገቱ ቀጣይነት ያለው እንዲሆን በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የታዳጊ ፕሮጀክቶችን በመክፈት ለፕሪሚየርሊጉ ክለቦች ተጫዋቾችን መጋቢ እንዲሆኑ እየተሰራ እንደሚገኝም አቶ ሞላ ተናግረዋል:: ፌዴሬሽኑ የሴቶች ፕርሚየርሊግንም ለመጀመርና በሴቶች የእጅ ኳስ ኢትዮጵያን በተለያዩ መድረኮች የሚወክል ቡድን ለመፍጠር እየሰራ እንደሆነ አክለዋል።

የ2015 የኢትዮጵያ እጅ ኳስ ፕርሚየርሊግ ውድድር ከታህሳስ 9/2015 ጀምሮ በአዲስ አበባ ትንሿ ስቴድየም እየተካሄደ ይገኛል:: ውድድሩ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ሳምንት በአዲስ አበባ እንደሚደረግና እስከ ታህሳስ 18 እንደሚቆይም ከፌዴሬሽኑ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። ፕሪሚየርሊጉ ዘንድሮ ለሰባተኛ ጊዜ የሚካሄድ ሲሆን አስር ክለቦችን ያፎካክራል:: ውድድሩ እስከ አራተኛ ሳምንት በአዲስ አበባ ተካሄዶ ወደ ሌሎች አዘጋጅ ከተሞች እንደሚያመራም ይጠበቃል። ከአራተኛ ሳምንት በኋላም ውድድሩን የሚያስተናግዱ ከተሞች ድሬዳዋና ባህርዳር ይሆናሉ:: በውድድሩ እየተሳተፉ የሚገኙ ክለቦች ቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ መቻል፣ አሜድላ፣ ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ፣ ባህርዳር ከነማ፣ ፌደራል ማረምያ፣ ከምባታ ዱራሜ፣ ፋሲል ከነማ፣ ሚዛን አማን ከተማና ድሬዳዋ ከተማ ናቸው:: ውድድሩ በዓመት በአጠቃላይ ዘጠና ጨዋታዎችን በማስተናገድ ፍጻሜውን የሚያገኝ ይሆናል::


## የተተው ዕቃዎች ግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ
## ቁጥር ገ-28/2015 ጨረታ

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አስመጪዎች በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 51 ንዑስ አንቀፅ 1 ወይም/እና አንቀፅ 156 ንዑስ አንቀፅ 4 ወይም/እና አንቀፅ 169 ንዑስ አንቀፅ 2 (በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 1160/2011 እንደተሻሻሉ ሆኖ) ወይም እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀፅ 168 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ዕቃቸውን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ፈጽመው ባለመውሰዳቸው ወይም የጉምሩክ ህግን በመተላለፋቸው ምክንያት ዕቃዎቹ እንደተተዉ ወይም እንደተወረሱ ተቆጥረዋል፡ ፡ ስለሆነም የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ
ጽ/ቤት የተተው ወይም የተወረሱ ዕቃዎችን በገቢዎች ሚኒስቴር የጉምሩክ ኮሚሽን በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ያሉ ንብረቶች ስለሚወገዱበት ሥርዓት ባወጣው መመሪያ ቁጥር 167/2012 አንቀጽ 9 መሠረት የተወረሱ ንብረቶችን ማለትም መስታወት፣ የሐይላንድ መስሪያ ግባቶች እና የሐይላንድ ክዳን፣ ወረቀት፣ የጎማ ክር፣ የቧንቧ ዕቃዎች፣ መጠቅለያ ወረቀት፣ ጁስ መፍጫ፣ የፕላስቲክ ወንበር፣ ነዳጅ፣ ፍራሽ፣ መብራቶች ኬሚካል እና የአረም መድሃኒት በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡
በዚህም መሠረት ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለመጫረት የሚፈልጉና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች በጨረታው መሳተፍ የሚችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

1. ተጫራቾች የዕቃዎቹን ዝርዝር ፣ ዓይነት ፣ ብዛት ፣ የጨረታ ሠነድ እና መመሪያ መግለጫ እንዲሁም የጨረታ ዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ ዘወትር ከሰኞ እስከ ሐሙስ ከጠዋት 2 00 እስከ ቀኑ 6፡00 ከሰዓት በኋላ ከቀኑ 7፡00 እስከ ቀኑ 10፡30 እና ዓርብ ከጠዋት 2፡00 እስከ ቀኑ 5:00 ከሰዓት በኋላ ከቀኑ 7:30 እስከ ቀኑ 10፡30 እንዲሁም ቅዳሜ ከጠዋት 2፡00 እስከ ቀኑ 5:30 የማይመለስ ብር 100 (አንድ መቶ) በመክፈል ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ገቢ ሂሳቦች ቡድን መውሰድ ይችላሉ፡፡
2. ተጫራቾች በጨረታ ከሚሸጠው ዕቃ ጋር በዘርፉ የፀና ንግድ ፈቃድ ያላቸው ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ምዝገባ ሰርተፍኬት እና የዘመኑን ግብር የከፈለ ለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት የተሰጠ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው:: ሆኖም ግምታዊ ዋጋቸው ከብር 500,000.00 በታች የሆኑ ማንኛውንም ዕቃ ለመግዛት የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ምዝገባ ሠርተፍኬት ማቅረብ ሳያስፈልግ መወዳደር ይችላሉ ::
3. ማንኛውም ተጫራች ለጨረታው ማስከበሪያ የሚሆን የሚጫረትበትን ጠቅላላ ዋጋ 5% ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ CPO ጨረታ ከመከፈቱ በፊት በቅድሚያ ማስያዝ ይኖርበታል:: ተሸናፊ ተጫራቾች ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ አሸናፊው እንደታወቀ በ3 (ሶስት) የሥራ ቀናት ውስጥ የሚመለስላቸው ሲሆን አሸናፊ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ከአሸነፈበት ዋጋ ላይ የሚታሰብላቸው ይሆናል:: ተጫራቾች የሚያስይዙት CPO በቅርጫፍ 8/01 ETHIOPIAN CUSTOMS COMMISSION MODJO BRANCH OFFICE በሚል ሲሆን የግል ባንክ ከሆነ ከአዲስ አበባ አስተዳደር ቅርጫፎች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከሆነ ደግሞ ከአዲስ አበባ አዳማ እና ሞጆ ቅርጫፎች መዘጋጀት አለበት ተሳታፊዎች ዋጋ ሙላት የሚችሉት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ተዘጋጅተው ማህተም ያረፈበት ሠነድ ላይ ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነድ በመግዛት የሚወዳደሩበትን ዕቃ አስቀድሞ ማየት ያለባቸው ሲሆን ዕቃውን ሳያዩ ለሚሞሉት ዋጋ ቅ/ጽ/ቤቱ ኃላፊነቱን አይወስድም፡፡
5. የግልፅ ጨረታ ተሳታፊ ተጫራቾች እያንዳንዱን ዕቃዎች ለመግዛት የሚያቀርቡት ዋጋ የሞሉበት ሠነድ፤ በተራ ቁጥር 2 የተገለፁትን ማስረጃዎች ኮፒ እና ያቀረቡ የመጫረቻ ዋጋ 5% ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ CPO በኤንቬሎፕ ወይም በፖስታ በማሸግ የጨረታ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ8 ተከታታይ ቀናት ጠዋት 4:45 ድረስ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ማስገባት ይቻላል፡፡
6 የጨረታ ሣጥኑ ከታሸገ በኋላ የሚመጡ የመጫረቻ ሰነዶች ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡
7. የጨረታ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጣበት ቀንን ጨምሮ በ8ኛው የሥራ ቀን ከጠዋቱ 4:45 ታሽጐ በዚሁ ዕለት ጠዋቱ 5፡00 ላይ ተጫራቾቹ ወይንም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለጨረታ በአዘጋጀው ቢሮ ውስጥ ይከፈታል፡፡
8. ማንኛውም በግልጸ ጨረታ የሚሳተፍ ተጫራች ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ዋጋ መቀየር ወይንም የሌላ ተጫራቾችን ዋጋ ተንተርሶ ዋጋ አሻሽሎ ማቅረብ አይችልም፡፡
9. ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ጨረታውን ለማሸነፍ ሲል የመደለያ የሰጠ ወይም ለመስጠት የሞከረ ማንኛውም ተጫራች ከጨረታው ይወገዳል ጨረታው ከተካሄደ በኋላም ቢሆን ጨረታ አሸናፊው ጨረታውን ያሸነፈው በህገ-ወጥ መንገድ መሆኑ ከተረጋገጠ የጨረታው ውጤት ይሰረዛል፡፡
10. ማንኛውም የጨረታ ሽያጭ የዕቃው አስመጪ ወይም ባለቤት እና ቤተሰብ የነበሩ ሰዎች በጨረታው መሳተፍ አይችሉም፡፡
11. ማንኛውም ተጫራች ጨረታው ከተከፈተ በኋላ እራሱን ከጨረታው ውድድር ማግለል አይቻልም፡፡
12. ማንኛውም ተጫራች የሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ የጨረታው ግምገማ ተጠናቆ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የጨረታውን ውጤት እስከሚያሳውቅ ድረስ ፀንቶ ይቆያል፡፡
13. የግልጽ ጨረታው አሸናፊ ጨረታውን ስለማሸነፋቸው ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በ5 (አምስት) ቀናት ውስጥ የአሸነፉበትን ዕቃ ዋጋ ገቢ በማድረግ ዕቃውን መረከብ አለበት በ5 (አምስት) ቀናት ውስጥ ገንዘቡ ገቢ ካልተደረገ ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ CPO ያስያዙት ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ይደረጋል፡፡ ያሸነፉት ዕቃም በድጋሚ ለጨረታ ሽያጭ ይቀርባል፡፡
14. በተራ ቁጥር 12 በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ የአሸነፉበትን ዕቃ ዋጋ ገቢ አድርጎ ዕቃውን ያላነሳ/ያልተረከበ እንደሆነ ለሚቆይበት ለተጨማሪ ጊዜ የመጋዘን ኪራይ ይከፍላል ሆኖም ዕቃው በ2 (ሁለት) ወራት ውስጥ ካልወጣ እንደተተወ ተቆጥሮ በጨረታ ሽያጭ ይወገዳል፡፡
15. አሸናፊው ተጫራቾች ዕቃዎችን ለመረከብና ለማጓጓዝ የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ሁሉ ራሱ ይሸፍናል፡፡
16. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለጨረታ የአቀረበውን ዕቃ ብዛት ለመጨመርም ሆነ ለመቀነስ ሙሉሙብት አለው::
17. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ዕቃዎቹን ለመሸጥ የተሻለ አማራጭ ወይም ዘዴ ከአገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
18 ለተጨማሪ ማብራሪያ በሥልክ ቁጥር 022-236-9094 ላይ ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**በገቢዎች ሚኒስቴር ጉምሩክ ኮሚሽን**
**የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**